የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፩
አዲስ አበባ ጥር ፳ ቀን ፪ሺ.፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No. 21
ADDIS ABABA 28th January, 2019

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፬፻፵፯/፪ሺ.፲፩ ዓ.ም

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢነርጂ ደንብ…ገጽ ፲ሺ.፱፻፰

## Content

Regulation No. 447/2019

Council of Ministers Energy Regulation……Page 10908

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፵፯/፪ሺ.፲፩

## ስለኢነርጂ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ.፺፯/፪ሺ.፲፩ አንቀጽ ፭ እና በኢነርጂ አዋጅ ቁጥር ፰፻፲/፪ሺ.፭ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ (፵)(፩) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢነርጂ ደንብ ቁጥር ፬፻፵፯/ ፪ሺ.፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ:-

፩/ "አዋጅ" ማለት የኢነርጂ አዋጅ ቁጥር ፰፻፲/፪ሺ.፭ (በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ.፹፭/፪ሺ.፲ እንደተሻሻለ) ነው፤

፪/ በአዋጁ የተመለከቱት ትርጓሜዎች በዚህ ደንብ ላይ ተፈጻሚ ናቸው፤

፫/ "የኢነርጂ ብቃት ውጤታማነት እርምጃ" ማለት የኢነርጂ ብቃትን ለማሻሻል የተወሰደ የአደረጃጀት፣ የቅርጽ፣ የቴክኒክ፣ የአፈጻጸም፣ የቴክኖሎጂ፣ የተቋም ወይም የቁጥጥር ለውጥ ነው፤

Council of Ministers Regulation No. 447/2019

## COUNCIL OF MINISTERS ENERGY REGULATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Power and Duty of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 1097/2018 and Article 40 (1) of the Energy Proclamation No. 810/2013 (as Amended).

## PART ONE
## GENERAL

**1. Short title**

This Regulation may be cited as the "Council of Ministers Energy Regulation No. 447/2019."

**2. Definitions**

In this Regulation:

1/"Proclamation" means the Energy Proclamation No. 810/2013 (Proclamation No.1085/2018 as Amended);

2/the definitions provided under the Proclamation is applicable to this Regulation.

3/"energy efficiency measure" means an organizational, structural, technical, performance, technological, institutional or regulatory change made for improving energy efficiency;

፬/ "የኢነርጂ ብቃት አገልግሎት" ማለት የኢነርጂ አገልግሎቱ ባለበት እንዲቀጥል ወይም እንዲጨምር ሆኖ የኢነርጂ ፍጆታ እንዲቀንስ የሚያስችሉ የምርመራ፣ የምክር፣ የጥናት፣ የንድፍ፣ የግንባታ፣ የኢንስታሌሽን፣ የማሻሻል፣ የመጠገን፣ የማስተዳደር እና የመቆጣጠር ተግባራትን በማሽን፣ በዕቃዎችና በሕንጻዎች ላይ ማከናወን ነው፡

፭/ "የአጭር ጊዜ ፕሮግራም" ማለት ከአንድ ዓመት እስከ ሦስት ዓመት ድረስ የሚሸፍን ፕሮግራም ነው፡

፮/ "የመካከለኛ ጊዜ ፕሮግራም" ማለት ከአራት ዓመት እስከ ስድስት ዓመት ድረስ የሚሸፍን ፕሮግራም ነው፡

፯/ "የረጅም ጊዜ ፕሮግራም" ማለት ከሰባት ዓመት እስከ አስር ዓመት ድረስ የሚሸፍን ፕሮግራም ነው፡

፰/ "ፋሲሊቲ" ማለት ለሥራቸው ኢነርጂ የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪን፣ ሕንጻን፣ ይዞታን እና ተያያዥ ኢንስታሌሽን እና መሣሪያዎችን ይጨምራል፡

፱/ "ኢንዱስትሪ" ማለት ለንግድ ዓላማ ዕቃዎችን በማምረት ተግባር የተሰማራ እና ለዚሁ ተግባር ኤሌክትሪክ የሚጠቀም ፋብሪካ ነው፡

፲/ "የተመረጠ ፋሲሊቲ" ማለት የኢነርጂ አጠቃቀምን መሠረት በማድረግ በባለሥልጣኑ በሚወጣ መመሪያ መሠረት የተመረጠ ኢንዱስትሪ ወይም ሕንጻ ነው፡

፲፩/ "የማመንጫ ፋሲሊቲ" ማለት ኤሌክትሪክን የሚያመነጭ የቴክኖሎጂ ስብስብ ነው፡

፲፪/ "ግሪድ ኮድ" ማለት የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት፣ የማስተላለፍ እና የማከፋፈል ሥርዓትን በሚመለከት አስፈላጊ የቴክኒክ አፈጻጸም መመዘኛዎችን የያዘ በባለስልጣኑ የሚወጣ ኮድ ነው፡

4/ "energy efficiency service" means activities of investigation, consulting, studying, designing, constructing, installation, rehabilitation, maintenance, management and monitoring of machinery, facilities and buildings resulting in reduction of energy consumption while retaining or increasing the energy service;

5/ "short-term program" means a program covering a period from one to three years;

6/ "medium-term program" means a program covering a period from four to six years;

7/ "long-term program" means a program covering a period from seven to ten years;

8/ "facility" includes industry, building, premises and associated installation and instruments that consume energy for its operations;

9/ "industry" means a factory engaged in the manufacturing of goods for commercial purpose and consume electricity for this purpose;

10/ "designated facility" means an industry or building designated by the Authority through directive to be issued hereunder based on energy consumption;

11/ "generation facility" means a set of technology used to produce electricity;

12/ "grid code" means a code issued by the Authority containing technical performance standards in relation to the power generation, transmission and distribution systems;

፲፫/ "ይዞታ" ማለት ከማናቸውም መሬት፣ ሕንጻ ወይም ግንባታ ጋር በተያያዘ የሚኖር እንደአግባቡ የመጠቀም ወይም የይዞታ መብት ነው፣

፲፬/ "የኔትወርክ አገልግሎት" ማለት የኤሌክትሪክ ኃይል የማስተላለፍ ወይም የማከፋፈል አገልግሎት ሲሆን የቮልቴጅ እና ፍሪኩዌንሲ መጠኑን ስምምነት ከተደረሰበት መጠን እንዳያልፍ ለመጠበቅ የሚያስችሉ ተጨማሪ አገልግሎቶችንም ያጠቃልላል፣

፲፭/ "ቆጣሪ" ማለት ማናቸውንም ተያያዥ እቃዎችን ጨምሮ የኤሌክትሪክ ፍጆታን የሚለካ መሣሪያ ነው፣

፲፮/ "ድጋፍ ሰጪ አገልግሎት" ማለት ኤሌክትሪክ ከማመንጨት እና ከማቅረብ ውጭ የሚሰጡ አገልግሎቶች ሲሆኑ የፍሪኩዌንሲ ቁጥጥርን፣ የመጠባበቂያ አቅም መጠን፣ የቮልቴጅ እና አፋጣኝ የኃይል ድጋፍ፣ ኤሌክትሪክ ከተቋረጠ በኋላ እንደገና የማስጀመር እና የኃይል ጭነት መጠን መቀነስን ወይም ማቋረጥን ያጠቃልላል፤

፲፯/ "ብቃቱ የተረጋገጠ ሰው" ማለት በዚህ ደንብ መሠረት ለኤሌክትሪክ ሥራ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ነው፤

፲፰/ "የብቻ ፈቃድ" ማለት ባለሥልጣኑ ለብቻ ፈቃድ በሰጠበት መልክዓ ምድራዊ አካባቢ ለተመሳሳይ ተግባር ሌላ ፈቃድ የማይሰጥበት ፈቃድ ዓይነት ነው፤

፲፱/ "የብቻ ያልሆነ ፈቃድ" ማለት በተመሳሳይ መልክዓ ምድራዊ አካባቢ ለተመሳሳይ ዓይነት ተግባራት እንዲያገለግል በተጨማሪ ፈቃድ ሊሰጥበት የሚችል የፈቃድ ዓይነት ነው፤

፳/ "አግባብ ያለው ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን" ማለት እንደየአግባቡ ባለሥልጣኑ ወይም ንግድ ሚኒስቴር ወይም ማናቸውም የክልል የንግድ፣ የኢንዱስትሪ ወይም የግንባታ ቢሮ ነው፤

13/ "premise" means as appropriate a use or possession right related to any land, building or structure;

14/ "network services" means electrical energy transmission or distribution services, including such ancillary services necessary to maintain voltage and frequency within the agreed limits;

15/ "meter" means a device, including any associated equipment, used for measuring electricity consumption;

16/ "ancillary service" means services such as frequency regulation, spinning reserves, voltage and reactive power support, black start and load shedding facilities, other than generation and supply of electricity;

17/ "certified person" means a person issued with a certificate of competency for electrical work pursuant to this Regulation;

18/ "exclusive license" means a type of license granted by the Authority and no other license may be granted for the same activity on the same geographical basis;

19/ "non-exclusive license" means a type of license granted by the Authority and additional licenses may be granted for the same kind of activities on the same geographical basis;

20/ "relevant licensing authority" means the Authority or Ministry of Trade or any of States Bureau of Trade, Industry or Construction as appropriate;

፳፩/ "ወቅታዊ ገበያ" ማለት ገዥዎች የኤሌክትሪክ ዋጋውን ለመክፈል የተዘጋጁበት እና ሻጮችም የኤሌክትሪክ ኃይሉን ለማስረከብ የተዘጋጁበት የኤሌክትሪክ የገበያ ሥርዓት ነው፤

፳፪/ "የግል ኃይል አመንጪ" ማለት በኃይል ግዥ ስምምነት ለብሔራዊ ግሪዱ ኤሌክትሪክ በጅምላ የሚሸጥ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ተቋም ባለቤት የሆነ ማናቸውም ሰው ነው፤

፳፫/ "ታዳሽ የኃይል ምንጭ" ማለት ኢነርጂ ለማመንጨት ጥቅም ላይ የሚውል እንደ ፀሀይ ብርሃን፣ ነፋስ፣ ውኃ እና የከርሰምድር እንፋሎት ያለ ታዳሽና የማያልቅ የተፈጥሮ ሀብት ነው፤

፳፬/ "ቁጥጥር የሚደረግበት መሠረታዊ ንብረት" ማለት በባለሥልጣኑ የእርጅና ቅናሽ ላይና የንብረት ተመላሽ ላይ በመመስረት ባለፈቃዱ ከሽያጭ ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ የሚያሰላበት በባለሥልጣኑ የተፈቀደ የባለፈቃዱ ንብረት ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ፈቃድ እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

### ፫. ስለማመልከቻ አቀራረብና ፈቃድ አሰጣጥ ጠቅላላ መስፈርቶች

፩/ ማናቸውንም ፈቃድ ለማግኘት ለባለሥልጣኑ የሚቀርብ ማመልከቻ ባለሥልጣኑ ለዚህ ዓላማ ያዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ከሚከተሉት የአመልካቹ መረጃዎች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡-

ሀ) የአመልካቹን ማንነት እና አድራሻ፤

ለ) የአመልካቹን የፋይናንስ አቅምና ሁኔታ፤

ሐ) የአመልካቹን የቴክኒክ ብቃት እና ልምድ፤

መ) የማመልከቻ መመርመሪያ ክፍያ ደረሰኝ፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ ለአመልካቹ ፈቃዱን መስጠት የሚችለው አመልካቹ ፈቃድ እንዲሰጠው በማመልከቻ የጠየቀውን የኤሌክትሪክ ተቋም ገንብቶ አገልግሎት ላይ የማዋል ብቃት ያለው መሆኑን በማረጋገጥ ይሆናል፡፡



21/ "spot market" means a system of electricity market that match the electricity at a price buyers are prepared to pay and sellers are prepared to deliver;

22/ "independent power producer" means any person that own generation plant and sell bulk electricity to the national grid through power purchase agreement;

23/ "renewable energy" means energy resources to be used for energy generation which are naturally replenished, such as sunlight, wind, water, and geothermal heat;

24/ "regulated basic asset " means an asset that is allowed by the Authority for the purpose of calculating the revenue requirement of the licensee based on the rate of return on assets and depreciation allowances of the authority.

## PART TWO

## LICENSE AND CERTIFICATE OF COMPETENCY

### 3. General Requirements for Application and Issuance of License

1/ Any application for a license shall be lodged to the Authority by filling the form prepared by the Authority for this purpose and accompanied with the following information of the applicant:

a) identity and address of the applicant;

b) documents showing the applicant's financial capacity and situation;

c) technical competency and experience of the applicant;

d) application examination fee receipt.

2/ The Authority shall issue the license to the applicant if verifies that the applicant is capable to construct and operate the electric supply system that he applied to obtain license.

፫/ ባለሥልጣኑ አመልካቹ ብቁ መሆኑን አረጋግጦ ፈቃድ ለመስጠት የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ሊያስገባ ይችላል:-

ሀ) አመልካቹ የቀድሞ እና የወቅቱ የንግድ ሥራዎቹንና እና ተያያዥ ሕጋዊ ግዴታዎቹን መፈጸሙንና ካልፈጸመም ምክንያቱን፣ እና

ለ) በአዋጁ መሠረት ፈቃድ በተሰጣቸው የንግድ ዘርፎች ላይ በማጭበርበር ወይም በተመሳሳይ ጥፋት በወንጀል ተከሶ አለመቀጣቱን፡፡

፬/ አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሰው ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከቱት ጉዳዮች ተፈጻሚነት የሚኖራቸው እንደየአግባቡ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል የሥራ ኃላፊዎች ላይም ይሆናል፡፡

፭/ በዚህ ደንብ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ተቋሙን ለማልማት፣ ለመገንባት፣ ለማሠራት ወይም ለመጠገን ተግባራዊ የሚሆኑ አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ሕጎችን የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

፮/ ባለሥልጣኑ አመልካቹ የጠየቀውን ፈቃድ የከለከለ እንደሆነ ፈቃዱን የከለከለበትን ምክንያት ለአመልካቹ በጽሁፍ መግለጽ እና ቅሬታ ካለው እንደገና እንዲታይለት ለመጠየቅ መብት እንዳለው ማሳወቅ አለበት፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሠረት የውሳኔው ማስታወቂያ የደረሰው አመልካች ቅሬታውን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለባለሥልጣኑ ቅሬታ ሰሚ አካል ማቅረብ ይችላል፡፡

፰/ ባለሥልጣኑ ከብሔራዊ ግሪድ ውጭ ስለሚሰሩ አነስተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት፣ የማከፋፈልና እና የመሸጥ ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓትን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፡፡

3/ The Authority may take into account the following conditions to verify the applicant's competence and to issue license:

a) compliance or any failure by the applicant to perform previous and current commercial or statutory obligations and the reasons in case of failure;

b) that he is not prosecuted and sentenced in relation to license issued as per the Proclamation for fraud or similar offence.

4/ If the applicant is a legal person, the provision of sub-article (3) of this Article shall also apply to the Directors of the body that have the legal personality.

5/ The applicant issued license pursuant to this Regulation shall also comply with the relevant laws as may be applied to the development, construction, operation or maintenance of such plant.

6/ If the Authority refuses to issue the license sought by the applicant, it shall promptly give the applicant a written notice informing the reasons for the refusal and the applicant's right to lodge complaint against the refusal.

7/ An applicant received refusal notice in accordance with sub-article (6) of this Article may file his complaints to the complaint handling body of the Authority within one month.

8/ The Authority shall issue a directive regarding the issuance of off grid small scale generation distribution and sale license.

፱/ የአዋጁ አንቀጽ ፮ (፪) እንደተጠበቀ ሆኖ ለንግድ ላልሆነ ዓላማ ኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት፣ ለማስተላለፍ ወይም ለማከፋፈል ፍላጎት ያለው ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ መሠረት መረጃዎችን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

## ፬. የፈቃድ ማመልከቻን ስለመመዝገብ

፩/ ባለሥልጣኑ የፈቃድ ማመልከቻ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ በተመለከተው መሠረት ተሟልቶ መቅረቡን በማረጋገጥ ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀው የምዝገባ ማመልከቻ መዝገብ ላይ እንደ ማመልከቻው ቅደም ተከተል በመመዝገብ ለአመልካቹ የምዝገባ ቀኑንና ቁጥሩን የሚገልጽ ደረሰኝ ይሰጣል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ የሚሰጠውን እያንዳንዱን ፈቃድ እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መዝግቦ መያዝ እና መዝገቡንም ለሕዝብ ክፍት ማድረግ አለበት፡፡

## ፭. የፈቃድ ማመልከቻን ይፋ ስለማድረግ

፩/ ባለሥልጣኑ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት በአመልካቹ ወጪ የፈቃድ ጥያቄውን ሰፊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ ወይም በሌሎች የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች አማካኝነት የሚከተሉትን መረጃዎች ይፋ ማድረግ አለበት፦

ሀ) ለፈቃድ ጥያቄ የቀረበውን ማመልከቻ እና የአመልካቹን ስም፣

ለ) ሚስጥራዊ ከሆኑ የንግድ መረጃዎች በስተቀር ኅብረተሰቡ ማመልከቻውን ከባለሥልጣኑ ቢሮ ቀርቦ ሊመለከት የሚችል መሆኑን፣

ሐ) የተጠየቀው ፈቃድ ቢሰጥ ጉዳት ይደርስብኛል የሚል ካለ በጋዜጣ ወይም በሌላ መገናኛ ብዙሃን ላይ በተገለጸ በ፴ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን በጽሁፍ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ የሚችል መሆኑን፡፡

9/ Without prejudice to Article 6(2) of the Proclamation, any person who has interest in the operations of generation, transmission or distribution of electricity for non-commercial purpose shall submit documents to the Authority in accordance with the Directive to be issued hereunder.

## 4. Registration of Application for License

1/ The Authority shall, upon verifying that the application for license is complete in accordance with article 3 of this Regulation, shall register the application in the registration book maintained for such purpose in the order of its submission and given a receipt to the applicant indicating the date and the number of the registration.

2/ The Authority shall maintain a register for licenses and certificates of competency issued and shall make open such register to the public.

## 5. Publication of License Application

1/ The Authority shall, before issuing a license, publicise the following information in a newspaper having wider circulation or other mass media by the expense of the applicant:

a) the application submitted for license and the name of the applicant;

b) possibility of inspection of the application in the office of the Authority by the public, except the confidential commercial information;

c) any person alleging that he may sustain damage due to the issuance of the requested license may lodge his objection in writing to the Authority within news paper or other mass midea 30 days from the date of issuance of the notice.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በወጣ ማስታወቂያ ላይ ተቃውሞ የቀረበ እንደሆነ ባለሥልጣኑ የሚመለከታቸው ወገኖች በስምምነት ለመጨረስ ድርድር እንዲያካሂዱ ያደርጋል፡፡

፫/ የቀረበውን ተቃውሞ አስመልክቶ ድርድር እንዲያካሂዱ ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ በ፴ ቀናት ውስጥ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች መስማማት ካልቻሉ፣ ባለሥልጣኑ የሁለቱንም ወገኖች ክርክር በመስማት የቀረበውን ተቃውሞ በመቀበል ወይም ውድቅ በማድረግ በ፴ ቀናት ውስጥ ውሣኔ ይሰጣል፡፡

## ፮. ማመልከቻን ስለማሻሻል

፩/ አመልካቹ በማመልከቻው ላይ ማናቸውንም ማሻሻያ ለማድረግ የፈለገ እንደሆነ ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ ማመልከት አለበት፡፡

፪/ ተሻሽሎ በቀረበው ማመልከቻ ላይ የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## ፯. የማመንጨት ፈቃድ ማመልከቻ

ማንኛውም ኤሌክትሪክ የማመንጨት ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ ከተመለከቱት ጠቅላላ መስፈርቶች በተጨማሪ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፦

፩/ በቅድሚያ የፈቃድ ማመልከቻ ጥያቄ ሲቀርብ፦

ሀ) የኤሌክትሪክ መገኛ ምንጩን፣

ለ) የፕሮጀክቱን ቦታ የሚያሳይ ካርታ፣

ሐ) የፕሮጀክቱን አጠቃላይ የማመንጨት አቅም በመለኪያ፣

መ) የሚገናኘውን የማስተላለፊያ ግሪድ ወይም የተያያዘ የአቅርቦት ኔትወርክ ወይም ከግሪድ ውጭ የሚሰራ ስለመሆኑ፣

ሠ) ቢያንስ የፕሮጀክት ቅድመ አዋጪነት ጥናት፣

ረ) የታቀደ የገንዘብ ምንጭ እና የብድር እና የመዋጮ ተነጻጻሪነት በመቶኛ፣



2/ If objection is lodged against issuance of the license in according to sub-article (1) of this Article, the Authority shall cause the concerned parties to settle the matter through negotiated agreement.

3/ If parties fail to reach agreement within 30 days after commencing negotiation, the Authority, after hearing the two parties, shall give a decision within 30 days either by accepting or rejecting the objection.

## 6. Amendment of Application

1/ If an applicant desires to make any amendment to his application, he shall submit a written application to the Authority.

2/ The provisions of this Part shall be applicable on the application amended.

## 7. Application for Generation License

Any application for a generation license shall, in addition to the general requirements stated under Article 3 of this Regulation, contain the following:

1/ Initially when submitting application for license:

a) source of electricity;

b) map of the project site;

c) total generation capacity of the project in measured units;

d) the transmission grid or supply network details to which it shall be connected or whether it operates on an off-grid basis;

e) at least prefeasibility study of the project;

f) planned source of finance, and proposed debt to equity ratio;

ሰ) ፈቃዱ ፀንቶ እንዲቆይ የሚፈለግበት ጊዜ፤እና

ሸ) ፈቃድ ሰጪው አስፈላጊ ናቸው ብሎ የመነባቸውን ሌሎች ተያያዥ ማስረጃዎች፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የቀረበ የፈቃድ ማመልከቻ ጥያቄ መሠረት ፈቃድ ሲሰጥ በፈቃዱ ላይ የተመለከተውን የንግድ ሥራ ከመጀመሩ በፊት:-

ሀ) እንደአግባቡ የፀደቀ የኃይል ግዥ ስምምነት፡

ለ) እንደአግባቡ የፕሮጀክት ፋይናንስ ስምምነት

ሐ) ከሚመለከተው አካል የአካባቢ ተጽዕኖ ሁኔታ ግምገማ ይሁንታ የምስክር ወረቀት፡

መ) እንደአግባቡ፣ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፡ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፡ የመሬት አጠቃቀም የምስክር ወረቀት፡ የውሃ መጠቀሚያ ፈቃድ፡ የከርሰምድር እንፋሎት ኃይል የማልማት ፈቃድ፡ ሌሎች ቀዳማይ የኢነርጂ ምንጮችን የማልማት ፈቃድ፡ እና የግንባታ ፈቃድ፣ ተሟልተው መቅረብ አለባቸው፡፡

## ፰. የኤሌክትሪክ ማስተላለፍ ፈቃድ ማመልከቻ

ከብሔራዊ ግሪዱ ጋር በተያያዘ ኤሌክትሪክ የማስተላለፍ ፈቃድ ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው መንግሥታዊ ተቋም ብቻ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የማስተላለፍ ፈቃድ ጥያቄ ማመልከቻው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ ከተመለከቱት አጠቃላይ መስፈርቶች በተጨማሪ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል:-

፩/ የማስተላለፊያ ግሪዱ የሚያልፍበት መስመር ካርታና የሥራ ቦታ፡

፪/ የፕሮጀክት አዋጪነት ጥናት፡

፫/ የማስተላለፊያ ግሪዱ ከሌላ ግሪድ ጋር የሚገናኝ ከሆነ የሚገናኘው ሌላኛው የማስተላለፊያ ግሪድ፡

g) proposed term of the license; and

h) other documents the licensing authority believes to be necessary and relevant.

2/ When a License is given after the application for license submitted in accordance with sub-article (1) of this article, the following shall be fulfilled before commencement of the licensed commercial activities:

a) approved power purchase agreement, where appropriate;

b) where applicable, project finance agreement

c) environmental impact assessment clearance certificate from the concerned authority;

d) trade registration certificate; tax payers identification number, land use permit, water use permit, geothermal resource development license, other primary energy resource development license, and construction permit as may be appropriate.

## 8. Application for Transmission License

Without prejudice to the sole right of the governmental organ to transmit power in the national grid, the application for transmission shall, in addition to the general requirements stated under Article 3 of this Regulation, contain the following in:

1/ route map and operation area of the transmission grid;

2/ project feasibility study;

3/ if the transmission line is to be connected to another transmission grid, the other transmission grid to which it may be connected;

፬/ ትክክለኛ የማስተላለፊያ ግሪዱ ወሰን፣

፭/ ሊገናኝ የሚችልበትን የአቅርቦት ኔትወርክ፣

፮/ ከሚመለከተው አካል የአካባቢ ተጽዕኖ ሁኔታ ግምገማ ይሁንታ የምስክር ወረቀት፣ እና

፯/ ፈቃዱ ፀንቶ እንዲቆይ የሚፈለግበት ጊዜ፡፡

፱. <u>ለኤሌክትሪክ ማከፋፈል እና መሸጥ ፈቃድ ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

በብሔራዊ ግሪዱ ውስጥ ኤሌክትሪክ የማከፋፈልና የመሸጥ ሥራ ለመሥራት ብቸኛ መብት ባለው የመንግሥት ተቋም ኤሌክትሪክ የማከፋፈል እና የመሸጥ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ ከተመለከቱት አጠቃላይ መስፈርቶች በተጨማሪ የሚከተሉትን መያዝ አለበት:-

፩/ የማከፋፈል ኔትወርክ የሚያልፍበት መስመር ካርታና እና የሥራ ቦታ፣

፪/ የፕሮጀክት አዋጪነት ጥናት፣

፫/ የማከፋፈል ሥራው ከሌላ የማከፋፈል እና የመሸጥ ኔትወርክ ጋር የሚገናኝ ከሆነ ሊገናኝ የሚችልበት የሌላኛው የማከፋፈል እና የመሸጥ ኔትወርክ ዋና ዋና መረጃዎች፣

፬/ ትክክለኛ የማከፋፈል እና የመሸጥ ኔትወርክ ወሰን፣

፭/ ሊገናኝ የሚችልበት የማስተላለፊያ ኔትወርክ ወይም የኤሌክትሪክ ምንጭ፣

፮/ እንደአግባቡ የኃይል ግዥ ስምምነት

፯/ ከሚመለከተው አካል የአካባቢ ተጽዕኖ ሁኔታ ግምገማ ይሁንታ የምስክር ወረቀት፣ እና

፰/ ፈቃዱ ፀንቶ እንዲቆይ የሚፈለግበት ጊዜ፡፡

፲. <u>ለኤሌክትሪክ አስመጪነት ወይም ላኪነት ፈቃድ ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

ኤሌክትሪክ ወደውጭ ሃገር ለመላክ ወይንም ከውጭ ሃገር ለማስገባት የሚቀርብ ማመልከቻ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ ከተመለከቱት አግባብ ካላቸው መስፈርቶች በተጨማሪ የሚከተሉትን መያዝ አለበት:-

4/ exact limit of the transmission grid;

5/ the supply network to which it may be connected;

6/ environmental impact assessment clearance certificate from the concerned authority; and

7/ proposed term of the license.

9. **<u>Application for Distribution and Sale License</u>**

The application for a distribution and sale license to be lodged by a public operator that has sole right to distribute and sale electricity in the national grid shall, in addition to the general requirements stated under Article 3 of this Regulation, shall contain the following:

1/ route map and operation area of the distribution network;

2/ project feasibility study;

3/ if the distribution network is to be connected to another distribution network the basic informations of other distribution network to which it may be connected;

4/ exact limit of the distribution network;

5/ the transmission network to which it may be connected or the source of electricity;

6/ power purchase agreement as appropriate;

7/ environmental impact assessment clearance certificate from the concerned authority and;

8/ proposed term of the license.

10. **<u>Application for Importation and Exportation of Electricity</u>**

Application for importation and exportation of electricity, in addition to the appropriate requirements stated under Article 3 of this regulation, shall fulfill the following:

፩/ ከብሔራዊ ግሪድ ኮድ ጋር የተጣጣመ መሆኑን የሚያረጋግጥ የቴክኒክ ደረጃ፣

፪/ እንደአግባቡ የኃይል ግዥ ስምምነት ወይንም የኃይል ማስተላለፍ አገልግሎት ስምምነት፣

፫/ እንደአግባቡ በወቅታዊ ገበያ ለመሳተፍ የሚያስችለው ተቀባይነት ያለው አግባብ ካለው ተቋም የተሰጠ ፈቃድ ወይንም የሰነድ ማስረጃ፣

፬/ ከሃገር ውስጥ ወደውጭ ሃገር እንዲላክ ወይንም ከውጭ ሃገር ወደሃገር ውስጥ እንዲገባ የሚፈለግ የኃይልና የኢነርጂ መጠንና ምንጩ፣

፭/ ወደውጭ ሃገር የሚላከው ወይንም ከውጭ ወደሃገር ውስጥ እንዲገባ የሚፈለገው የኃይል መጠን በተገልጋዮችና በኢኮኖሚው ላይ ሊያሳድር የሚችለው አንደምታ፣ እና

፮/ እንደአግባቡ ኤሌክትሪክ ከሚያስመጣበት ወይንም ከሚልክበት ሃገር ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የተደረገ ስምምነት፡፡

**፲፩. <u>ስለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ</u>**

፩/ ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳይሰጠው የኤሌክትሪክ ሥራ ተግባራትን ማከናወን አይችልም፡፡

፪/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት በባለሙያ የሚቀርብ ማናቸውም ማመልከቻ ከዝርዝር የቴክኒክ መስፈርቶችና መረጃዎች በተጨማሪ የሚከተሉትን መያዝ አለበት:-

ሀ) የአመልካቹን ማንነት እና አድራሻ፣

ለ) የትምህርት ደረጃ፣ እና

ሐ) እንደአስፈላጊነቱ የሥራ ልምድ፡፡

፫/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት በድርጅት የሚቀርብ ማናቸውም ማመልከቻ ከዝርዝር የቴክኒክ መስፈርቶችና መረጃዎች በተጨማሪ የሚከተሉትን መያዝ አለበት:-

ሀ) የአመልካቹን አድራሻ፣

ለ) በቋሚነት ስለተቀጠሩ ብቁ ባለሙያዎች፣

ሐ) እንደአግባቡ የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ፡፡

1/ technical standard compatible with that of the national Grid Code;

2/ power purchase agreement or transmission service agreement as may be applicable;

3/ as may be applicable acceptable license or document issued by the appropriate Authority where by the applicant may participate in a spot market;

4/ source and amount of desired import or export of power and energy;

5/ possible impact of the desired import or export on existing customers and the economy; and

6/ as may be applicable agreements with entities in the country where the electricity is to be imported or exported.

**11. <u>Issuance of Certificate of Competency</u>**

1/ No person shall undertake electrical work activities without obtaining certificate of competency from the Authority.

2/ Any application submitted for a certificate of competence by a professional, in addition to the detailed technical criteria and document, shall contain the following:

a) identity and address of the applicant;

b) level of education; and

c) work experience, as appropriate.

3/ Any application submitted for a certificate of competence by a business organization, in addition to the detailed technical criteria and documents, shall contain the following:

a) address of the applicant;

b) qualified staffs employed in a permanent basis;

c) Memorandum of association and article of association, as appropriate.

፬/ አመልካች ማመልከቻውን በዚህ ደንብ በሰንጠረዥ ፩ ከተገለፀው የማመልከቻ መመርመሪያና የምዝገባ ክፍያ ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

፭/ ባለሥልጣኑ አመልካች ከማመልከቻው ጋር አያይዞ ያቀረባቸውን መረጃዎች ትክክለኛነት መርምሮ ካረጋገጠ በኋላ አመልካቹ ላመለከተበት የምስክር ወረቀት ደረጃ ብቁ ስለመሆኑ ለመወሰን እንደአግባቡ የጽሁፍ እና የተግባር ፈተና ሊሰጥ ይችላል፡፡

፮/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስፈርቶች መሟላታቸውን ያረጋገጠ እንደሆነ በዚህ ደንብ በሰንጠረዥ ፩ የተገለፀውን የምስክር ወረቀት ክፍያ በማስከፈል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ለአመልካቹ መስጠት አለበት፡፡

፯/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለመስጠት የሚያስፈልጉ ዝርዝር የቴክኒክ መስፈርቶችና መረጃዎች ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

፰/ ባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጠው የጠየቀው ሰው ያቀረበው መረጃ በቂ አይደለም ብሎ ከወሰነ ይህንኑ ውሳኔ ለአመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

**፲፪. ፈቃዱ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ እና እድሳት**

፩/ በአዋጁ እና በዚህ ደንብ መሠረት የሚሰጥ ፈቃድ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንደሚከተለው ይሆናል:-

ሀ) ለውኃ እና ለጂኦተርማል ኃይል ማመንጫ ፈቃድ እስከ ፳፭ ዓመት፣

ለ) ለነፋስ፣ ለፀሐይ፣ ለባዮማስ፣ ለከተማ ቆሻሻ፣ ለተርማል እና ለባዮጋዝ ኃይል ማመንጫ ፈቃድ እስከ ፳ ዓመት፣

ሐ) ለማስተላለፍ ፈቃድ እስከ ፴ ዓመት፣ እና

መ) ለማከፋፈል እና ለመሸጥ ፈቃድ እስከ ፳ ዓመት፡፡

4/ The applicant's Application shall be accompanied by application examination and registration fee prescribed under Table 1 of this Regulation.

5/ The Authority may, following verification of informations submitted in connection with the application, give a written and practical examination, as may be appropriate, to evaluate the competency of the applicant and to determine whether the applicant qualify to the grade of the certificate applied.

6/ Where the Authority prove that the applicant has fulfilled the requirements of certificate of competency; it shall issue a certificate of competency to the applicant upon the payment of the fees prescribed under Table 1 of this Regulation.

7/ Detailed technical criteria and documents required to issue certificate of competency shall be determined by a directive to be issued to implement this Regulation.

8/ If the Authority decides that the information submitted by the applicant certificate of competency is inadequate it shall notify its decision to the applicant in writing.

**12. Validity Period and Renewal of License**

1/ The validity period of license issued pursuant to the provisions of the Proclamation and this Regulation shall be as follows:

a) hydro and geothermal power generation license up to 25 years;

b) wind, solar, bio-mass, urban waste, thermal and bio-gas power generation license up to 20 years;

c) transmission license up to 30 years; and

d) distribution and sale license up to 20 years.

፪/ በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ፈቃድ ሊታደስ የሚችለው ባለፈቃዱ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ሲያሟላ ብቻ ይሆናል:-

ሀ) የፈቃድ ጊዜው ከማብቃቱ ከአንድ ዓመት በፊት ሲያመለክት እና ፋሲሊቲዎች በጥሩ የሥራ ሁኔታ ላይ ስለመሆናቸው በባለሥልጣኑ ሲረጋገጥ፤

ለ) ባለፈቃዱ ለፈቃድ መሠረዝ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ማናቸውንም የአዋጁን፣ የዚህን ደንብ እና ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚወጣ መመሪያ ድንጋጌዎችን ያልጣሰ ከሆነ፣ እና

ሐ) በኃይል ኢንደስትሪ ውስጥ በአጠቃላይ ተቀባይነት ባገኘ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ መሠረት ሥራዎችን ለማሳደግ የተስማማ ከሆነ፡፡

፫/ እያንዳንዱ የፈቃድ እድሳት ጊዜ ፈቃዱ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሰጥ ጸንቶ እንዲቆይ የተደረገበት ዓመታት ካበቃ በኋላ እንደሚከተለው ይሆናል:-

ሀ) ለውኃ ኃይል ማመንጫ ፈቃድ እስከ ፲፪ ዓመት ከ፮ ወር፤

ለ) ለነፋስ፣ ለፀሀይ፣ ለባዮማስ፣ ለከተማ ቆሻሻ፣ ለተርማል እና ለባዮጋዝ ኃይል ማመንጫ ፈቃድ እስከ ፲ ዓመት፤

ሐ) ለማስተላለፍ ፈቃድ እስከ ፲፭ ዓመት፤

መ) ለማከፋፈል እና ለመሸጥ ፈቃድ እስከ ፲ ዓመት፡፡

፬/ የኤሌክትሪክ ኃይልን ወደውጭ ሃገር ለመላክ ወይንም ከውጭ ሃገር ለማስመጣት የሚሰጥ ፈቃድ ዘመን እና የእድሳት ጊዜ በዚህ አንቀጽ ለማስተላለፊያና እንደአግባቡም ለማከፋፈልና ለመሸጥ ከተቀመጠው ፈቃድ ዘመን ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

2/ unless stated otherwise in other laws a license, may be renewed only when the licensee:

a) has made an application one year prior to the expiry of the term of license and the Authority proves that the facilities are in good working condition;

b) was not in breach of any provisions of the Proclamation, this Regulation and directive issued hereunder which constitutes as grounds for revocation of license; and

c) has agreed to upgrade operations in accordance with latest technology generally accepted in the power industry.

3/ After the validity period of the license each renewal period of license shall be as follows:

a) hydro power generation license, up to 12 years and 6 months;

b) wind, solar, bio-mass, urban waste, thermal and bio-gas power generation license, up to 10 years;

c) transmission license, up to 15 years; and

d) distribution and sale license, up to 10 years.

4/ The validity and renewal period of import or export license of electricity power shall be similar to that of the transmission and as may be appropriate, that of the distribution and sales license.

**፲፫. ፈቃድን ስለማሻሻል**

፩/ ፈቃዱን ለማሻሻል የሚፈልግ ማንኛውም ባለፈቃድ የጽሁፍ ማመልከቻ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የቀረበ ማመልከቻ ላይ የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ቅጽ ተሞልቶ ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር ለባለሥልጣኑ መቅረብ አለበት፦

ሀ) የነባሩ ፈቃድ ቅጂ፤

ለ) ማመልከቻው የቀረበው በወኪል ከሆነ የውክልና ማስረጃ ቅጂ፤

ሐ) ኢንቨስትመንቱ የሚፈጸመው በንግድ ማኅበር ሲሆን የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ቅጂ፤ እና

መ) ሌሎች በባለሥልጣኑ መመሪያ የተወሰኑ ሰነዶች፡፡

፬/ ማንኛውም ሰው በተመሳሳይ ሥራ በተለያየ ቦታ ለመሰማራት ወይም ሥራውን ለብቻ ፈቃድ ካልሆነ አካባቢ ውጭ ለማስፋፋት ሲወስን አዲስ ፈቃድ ማውጣት አለበት፡፡

**፲፬. ፈቃድን ስለማስተላለፍ**

ማንኛውም ባለፈቃድ ፈቃዱን ሊያስተላልፍ የሚችለው ፈቃዱ የሚተላለፍለት ሰው በፈቃዱ የተመለከቱትን ግዴታዎች ለመወጣት የሚያስችል ብቃት ያለው ስለመሆኑ በባለሥልጣኑ ሲረጋገጥ ይሆናል፡፡

**፲፭ የፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ስለማገድ ወይም ስለመሰረዝ**

፩/ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ፈቃድ ሊታገድ ይችላል፦

**13. Amendment of License**

1/ Any licensee who desires amendment of his license shall submit a written application to the Authority.

2/ The provisions of this Part shall be applicable on the application made for amendment pursuant to sub-article (1) of this Article.

3/ The application submitted for amendment pursuant to sub-article (1) of this Article shall be made by filling a form designed for such purpose and submitted to the Authority together with the following documents:

a) copy of the previous license;

b) when the application is submitted by an agent, copy of the power of attorney;

c) where the investment is made by business organization, copy of its commercial registration certificate; and

d) such other documents determined in the directive of the Authority.

4/ A new license shall be required if a person decides to engage in a similar operation at a different location or to extend its operation beyond the boundary of its non-exclusive licensed area of operation.

**14. Transfer of License**

Any licensee may transfer his license, when the Authority confirms that the one to whom the license to be transferred, has the required competency to fulfill the obligations of the license.

**15. Suspension or Revocation of License or Certificate of Competency**

1/ A license may be suspended on one of the following grounds:

ሀ) በባለስልጣኑ ከተሰጠው ደረጃ ውጭ መሠረታዊ የአገልግሎት አቅርቦት ጥራት ጉድለት ወይም የደህንነት ጉድለት ሲፈጠርና በተሰጠው የማስተካከያ ጊዜ ውስጥ የእርምት እርምጃ ያልወሰደ እንደሆነ፣

ለ) በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት ማቅረብ የሚገባውን ሪፖርት አሟልቶ ያላቀረበ ወይም የተሳሳተ ሪፖርት ያቀረበ እንደሆነ ወይም አስፈላጊ ሰነዶችን ሳይዝ የቀረ እንደሆነ፤

ሐ) የባለሥልጣኑ የቁጥጥር ሥራ እንዳይከናወን ሆን ብሎ ያሰናከለ ወይም ያወከ እንደሆነ፤

መ) ከባለሥልጣኑ እውቅና ውጭ ለሦስተኛ ወገን ፈቃዱን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፣ ወይም

ሠ) የማመንጫ ባለፈቃድ ሲሆን፣ የፈቃድ ስምምነቱ በሚጠይቀው መሠረት የታደሰ የኃይል ግዥ ስምምነት ያላቀረበ እንደሆነ፡፡

፪/ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊታገድ ይችላል:-

ሀ) በብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ላይ ከተፈቀደው ሥራ ውጭ መሰማራት ወይም ደረጃውን ያልጠበቀ ሥራ መስራት፤

ለ) የሰራው ሥራ መሠረታዊ በሆነ የደህንነትና የጥራት ችግር ምክንያት በተገልጋዩ ላይ የህይወት ወይም የንብረት አደጋ መፍጠር፤

ሐ) በዚህ ደንብ መሠረት መቅረብ የሚገባውን ሪፖርት ሳያሟላ ማቅረብ ወይም የተሳሳተ ሪፖርት ማቅረብ ወይም አስፈላጊ ሰነዶችን አለመያዝ፤

መ) የባለስልጣኑ የቁጥጥር ሥራ እንዳይከናወን ሆን ብሎ ማሰናከል ወይም ማወክ፣ እና

ሠ) በባለሥልጣኑ የተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት፡፡

a) failure to maintain the basic service supply quality standard or safety standard issued by the Authority and inability to rectify the situation with in the time limit given by the Authority;

b) fails to submit a complete report in accordance with the provisions of this Regulation or submits false report or fails to maintain proper documentations;

c) intentionally obstructs or creates obstacle in the regulatory activities of the Authority;

d) transfers his license to a third party without the consent of the Authority; or

e) a generation licensee, if fails to submit a renewed power purchase agreement in accordance with the terms of the license.

2/ Acertificate of competence may be suspended on one of the following grounds:

a) engaging in activities beyond authorized in the certificate of competence issued by the Authority or perform below the standard;

b) cause damage on life or property of the service user as a result of basic safety and quality problem of the work performed;

c) submit incomplete or false report or failure to maintain appropriate documentations in accordance with this Regulation;

d) intentionally obstruct or creates obstacle in the regulatory activities of the Authority; and

e) transfer his certificate of competence to a third party.

፫/ ባለሥልጣኑ ፈቃድን ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ከማገዱ በፊት ለማገጃ ምክንያት የሆኑ ጉዳዮችን በመግለጽ ቢያንስ ከ፵፭ (አርባ አምስት) ቀናት በፊት ለባፈቃዱ ወይም ለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለቤቱ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት አለበት፡፡

፬/ ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የታገደበት ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፫) መሠረት በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማስተካከያ እርምጃ ያልወሰደ እንደሆነ ወይም በሁለት ዓመት ውስጥ እገዳን ሊያስከትል የሚችል ሌላ ጥፋት ደግሞ የመፈጸመ እንደሆነ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

፭/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት በሚሰጠው የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ውስጥ ባለፈቃዱ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ባለቤቱ የሚወስደውን እርምጃ ወይም የመፍትሔ ሀሳብን ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ እንዲያቀርብ ማሳወቅ አለበት፡፡

፮/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፰) የተመለከተው ጊዜ እንዳበቃ፦

ሀ) ማናቸውንም ፈቃድ በሙሉ ወይም በከፊል ሲያግድ ወይም ሲሰርዝ ስለእገዳው ወይም ስለስረዛው ሰፊ ስርጭት ባለው መገናኛ ብዙሃን ለሕዝብ ይፋ ማድረግ አለበት፡፡

ለ) ማናቸውንም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በሙሉ ወይም በከፊል ሲያግድ ወይም ሲሰርዝ ስለእገዳው ወይም ስለስረዛው ሰፊ ስርጭት ባለው መገናኛ ብዙሃን ለሕዝብ ይፋ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፯/ ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ወይንም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ለማገድ ሲወስን ፈቃዱ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ በመታገዱ ወይም በመሰረዙ ምክንያት በማንኛውም ሰው ላይ ሊደርስ የሚችለውን የጉዳት መጠን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

፰/ ፈቃዱ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ማንኛውም ሰው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔው እንደገና እንዲታይለት በጽሁፍ ለባለስልጣኑ ማመልከት ይችላል፡፡

3/ The Authority shall, at least 45 (forty five) days ahead, issue a written notice to the holder of the license or certificate by stating the grounds on which suspension or revocation measure is to be taken.

4/ A license or certificate of competence of any person may be revoked accordance with sub-article(3) of this article, if the person fails to rectify the problem entailed suspension within the period given to rectify it, or commits another problem for the second time within two years which may entail suspension.

5/ The notice served by the authority in accordance with sub-article (3) of this Article, shall notify the holder of a license or certificate to submit in writing the measure that he is going to take or express his opinion in writing to the Authority.

6/ The Authority, after the laps of period stated under sub-article (8) of this Article, where it;

a) suspends or revokes any license either in whole or in part, it shall publish such suspension or revocation on a mass media having wider circulation

b) suspends or revokes any competency certificate either in whole or in part, it may publish such suspension or revocation on a mass media having wider circulation.

7/ The Authority shall take into consideration in its decision to suspend or revoke a license or competency certificate, the extent to which any person is likely to suffer damage as a result of suspension or revocation of a license.

8/ Any person whose license or certificate of competency suspended or.revoked by the Authority may apply to the Authority within one month for review of the decision by the Authority.

፲፮. **<u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጸንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ እና እድሳት</u>**

፩/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለሁለት ዓመታት ጸንቶ ይቆያል፡፡

፪/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ከማብቃቱ ቢያንስ ከ፲፭ (ከአስራ አምስት) ቀናት በፊት ከማመልከቻ ጋር ቀርቦ መታደስ አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተመለከተው ጊዜ ገደብ ውስጥ የምስክር ወረቀቱ ሳይታደስ ጊዜው ያለፈበት ማንኛውም ሰው የእድሳት ዘመኑ ካበቃ በኋላ ቀጥሎ ባሉት ፺(ዘጠና) ቀናት ውስጥ የምስክር ወረቀቱ እንዲታደስለት ለባለሥልጣኑ ሊያመለከት የሚችል ሲሆን፣ ባለሥልጣኑም በመመሪያ በሚወሰን መሠረት ቅጣት አስከፍሎ፣ ሊያድስ ይችላል፡፡

፬/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ባለሙያ የምስክር ወረቀቱን ለማሳደስ ሲቀርብ የምስክር ወረቀቱ ጸንቶ በቆየበት ጊዜ ውስጥ ቢያንስ ለሦስት ወራት ያህል የሥራ ልምድ ያገኘበትን የሚገልጽ ማስረጃ ወይም ከብቃት ማስረጃው ጋር ግንኙነት ባለው ተከታታይ የስልጠና ፕሮግራም ለ፲፮ ሰዓታት ሥልጠና መካፈሉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

፭/ ማንኛውም ብቃቱ የተረጋገጠ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ለማሳደስ ሲቀርብ የድርጅቱን ባለሙያዎች የትምህርት ማስረጃ ከነብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ እና አስፈላጊ ከሆኑ ሌሎች ሰነዶች ጋር በማያያዝ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

፲፯. **<u>ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመተካት</u>**

፩/ ማንኛውም ባለፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው በዚህ ደንብ በሰንጠረዥ ፩ የተወሰነውን የማመልከቻና የምዝገባ ክፍያ በመክፈል የጠፋበትን ወይም የተበላሸበትን ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ምትክ እንዲሰጠው ለባለሥልጣኑ ሊያመለከት ይችላል፡፡

16. **<u>Validity Period and Renewal of Certificate of Competency</u>**

1/ A certificate of competency shall be valid for two years starting from the date of its issuance.

2/ A certificate of competency shall be renewed at least 15 (fifteen) days before its expiry date by submitting application for its renewal.

3/ Any person whose certificate of competency has not been renewed within the period specified under sub-article (2) of this Article, may apply for renewal within subsequent 90(ninety) days of its expiry and the Authority may renew the certificate upon payment of penalty fee to be prescribed in a directive.

4/ Any professional who wants to renew his certificate of competency shall produce evidence showing that, within the validity period of the certificate, that he has at least gained three months work experience or has participate at least for 16 hours training which has relevance to the certificate issued.

5/ Any certified business organization requests to renew its certificate of competency shall present its professional staff and their respective certificate of competence together with other relevant documents to the authority.

17. **<u>Replacement of License or Certificate of Competency</u>**

1/ Any licensee or holder of certificate of competence may, upon the payment of the application and registration fee prescribed on the table 1 of this Regulation, may apply to the Authority for the replacement of the license or certificate of competency, which has been lost or destroyed.

፪/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ማመልከቻውን ከተቀበለ በኋላ አግባብ ያለውን ማጣራት አካሂዶ ምትክ ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

**፲፰. ቁጥጥር ስለማካሄድ**

፩/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው በምስክር ወረቀቱ መሠረት ሥራውን እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ባለሥልጣኑ ተቆጣጣሪ ሠራተኛ ይመድባል፡፡

፪/ በባለሥልጣኑ የተመደበ ተቆጣጣሪ ሠራተኛ የቁጥጥር ተግባሩን በሚያከናውንበት ጊዜ ከባለሥልጣኑ የተሰጠውን መታወቂያ በማሳየት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያለውን ሰው እንደአግባቡ ሰነዶችን፣ መዝገቦችን፣ ማሽኖችን፣ የመገልገያ መሣሪያዎችን እና ሌሎች በእጁ ያሉ መረጃዎችን ሊጠይቅ እና ሊመረምር ይችላል፡፡

፫/ ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው በብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ስለተከናወኑ ተግባራት ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ መሠረት ባለሥልጣኑ ያዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት የማጠናቀቂያ ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

**፲፱. ስለፈቃድ እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መሰረዝ**

ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በሚከተሉት ሁኔታዎች ይሰረዛል፤

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፪ እና አንቀጽ ፲፮ መሠረት ያልታደሰ እንደሆነ፤ወይም

፪/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፭ መሠረት በባለሥልጣኑ የተሰረዘ እንደሆነ፤ ወይም

፫/ የወራሾች መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ባለፈቃዱ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኘ ግለሰብ የሞተ እንደሆነ ወይም የንግድ ድርጅት ሲሆን የፈረሰ ወይም የመክሰር ውሳኔ የተሰጠበት እንደሆነ፡፡

2/ The Authority after receiving the application in accordance with sub-Article (1) of this Article shall issue a replaced license or certificate of competency, after conducting appropriate verification.

**18. Inspection**

1/ The Authority shall assign inspection officer to supervise the activities of a certificate of competency holder whether he conducts its work in accordance with the terms of certificate of competence.

2/ The inspection officer assigned by the Authority shall show his identification card issued by the Authority while conducting inspection, and may require the certified person to submit documents, records, machineries, tools, any other informations at its disposal, as appropriate.

3/ Any certified person shall submit a completion report to the Authority on tasks performed with the certificate of competence issued, by filling form prepared by the Authority in accordance with directive to be issued to implement this regulation.

**19. revocation of License and Certificate of Competency**

A license or certificate of competency shall revoked if:

1/ it expires without being renewed pursuant to Article 12 and Article 16 of this Regulation;

2/ it is revoked by the Authority pursuant to Article 15 of this Regulation; or

3/ without prejudice to the rights of heirs, a license or certificate of competency shall be terminated when an individual dies or when a business organization is liquidated or declared bankrupt.

**፳. ስለፈቃድ እና ስለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ክፍያ**

ፈቃድ መስጠትን፣ ማስተዳደርን እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን በተመለከተ ባለሥልጣኑ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚፈጸሙ ክፍያዎች የአገልግሎት ክፍያን በተመለከተ በዚህ ደንብ በሰንጠረዥ ፩ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት
## መብትና ግዴታ

**፳፩. የባለፈቃዱ መብቶች**

ማንኛውም ባለፈቃድ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል:-

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፪(፱) ላይ ከተደነገገው መጠን በታች የሆነ መዋዕለ ንዋይ እንዲጸድቅለት በራሱ ፍላጎት ለባለሥልጣኑ የማቅረብ፣

፪/ በፀደቀው ታሪፍ መሠረት ገቢውን የመሰብሰብ፣

፫/ በአዋጁ አንቀጽ ፲፮ መሠረት የኤሌክትሪክ አቅርቦት ሥራዎችን ለማካሄድ በደንበኛው ይዞታ ውስጥ የመግባት፣

፬/ በአዋጁ አንቀጽ ፲፪ መሠረት የደንበኞችን የኤሌክትሪክ አገልግሎት የማቋረጥ፣ እና

፭/ የደንበኞችን የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽኖችን የመመርመር፡፡

**፳፪. የባለፈቃዱ ግዴታዎች**

ማንኛውም ባለፈቃድ በአዋጁ አንቀጽ ፲ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ግዴታዎች አለበት:-

፩/ በአዋጁ፣ በዚህ ደንብ እና ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጡ መመሪያዎች እና የፈቃድ ሁኔታዎች መሠረት የኤሌክትሪክ አቅርቦት ሥራዎችን የማካሄድ፣

**20. Fee for License and Certificate of Competency**

The service fees to be paid for the Authority with regards to the issuance and administering of the license and certificate of competency shall be as per the provisions of Table 1 of this regulation.

## PART THREE
## RIGHTS AND OBLIGATIONS

**21. Right of Licensee**

Any licensee shall have the following rights:

1/ seek approval, on its own discretion, of investment which is below the amount indicated under Article 22(9) of this Regulation;

2/ collect revenues in accordance with approved tariffs;

3/ enter into the premises of the customer, in accordance with Article 16 of the Proclamation, to undertake electricity supply operations;

4/ disconnect electricity service of customers in accordance with Article 12 of the Proclamation; and

5/ examine electric installations of the customers.

**22. Obligations of Licensee**

Without prejudice to Article 10 of the proclamation Any licensee shall, have the following obligations:

1/ carry out electricity supply operations in accordance with the provisions of the Proclamation, this Regulation and directives issued to implement this regulation and conditions of the license;

፪/ የፈቃዱን ተግባራት ለመጀመር የሚያስፈልጉትን ፋሲሊቲዎች ባለሥልጣኑ በሚያወጣው የግሪድ ኮድና ሌሎች አሠራሮች መሠረት የማሟላት፤

፫/ ሁሉንም የቅጥር፣ የገንዘብ፣ የንግድና ሌሎች መዛግብትን እና ሪከርዶችን እንዲሁም የኤሌክትሪክ ሥራዎችን መዛግብቶች ቢያንስ ለ፲ ዓመታት የመያዝ፤

፬/ ዕቅድን፣ መረጃን እና ሪፖርቶችን በዚህ ደንብ እና ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ የአሠራር ሥርዓት በተወሰነው መሠረት የማቅረብ፤

፭/ የግንባታ ፕላንና ሪፖርት የማቅረብ፤

፮/ የንግድ ሥራውን በብቃት ለመምራት የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን፣ ሥርዓቶችን እና የአስተዳደር ዘዴዎችን ተግባራዊ ማድረግ እና ይህም አግባብነት ካላቸው ከሠራተኞች ጤና እና ደህንነት፣ ከሕዝብ፣ ከአካባቢ እና ከተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሕጎች ጋር የተጣጣመ ስለመሆኑ ለባለሥልጣኑ መረጃ የማቅረብ፤

፯/ የሰውን ህይወት፣ ንብረት፣ የአካባቢ እና የተፈጥሮ ሀብት ደህንነትን ለመጠበቅ የጥንቃቄ እርምጃ የመውሰድ፤

፰/ በኤሌክትሪክ አቅርቦት የያዘውን የብቸኛነት ቦታ ከፍተኛ ታሪፍ ለማስከፈል ወይም የወጪ ቅነሳ ብቃት እርምጃዎች እንዳይከተቱ ለማድረግ አለመጠቀም፤

፱/ ባለሥልጣኑ ባፀደቀው የኃይል ግዥ ስምምነት ወይም በባለሥልጣኑ በተፈረመ ሌላ ስምምነት ላይ ካልተመለከተ በስተቀር በፈቃዱ ከተሸፈነውና ቁጥጥር ከሚደረግበት ሀብት ከ፲ በመቶ (ከአስር በመቶ) ዋጋ በላይ ለሚያደርገው የመዋዕለ ነዋይ ኢንቨስትመንት በቅድሚያ በባለሥልጣኑ እንዲፀድቅ የማድረግ፤

2/ fulfill facilities in accordance with the Grid Code and other related procedures to be issued by the Authority, in order to commence activities licensed;

3/ keep all employment, financial, commercial and other books and records as well as records of electricity operations at least for 10 years;

4/ submit plan, information and reports as determined in this Regulation and directive and procedures issued hereunder;

5/ sumbit construction plan and report;

6/ submit evidence to the Authority that it has introduced appropriate policies, procedures and management systems for the efficient commercial operation of its business and that allow compliance with all relevant Regulation of health and safety of the employees; the public, environment and natural resources;

7/ take appropriate measures in order to protect human life, property, the environment and natural resources;

8/ not exploit its monopoly position held in the supply of electricity to maintain high tariffs or to avoid the introduction of cost efficiency measures;

9/ unless otherwise agreed to in a power purchase or other agreement approved of or acceded to by the Authority, seek prior approval from the Authority for all investments that exceed a value to the equivalent of 10% (ten perecent) of the regulated asset;

፲/ ለሠራተኞቹ አግባብ ያለው ሥልጠና የመስጠት፤

፲፩/ አግባብ ባለው አካል በፀደቀ ታሪፍና የኃይል ግዥ ስምምነት መሠረት ብቻ ክፍያ የመሰብሰብ፤

፲፪/ በባለሥልጣኑ የሚሰጡ ሁሉንም ማስታወቂያ ዎች ተግባራዊ የማድረግ፤ እና

፲፫/ የተሰረዘበትን ፈቃድ ለባለስልጣኑ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የመመለስ፡፡

፳፫. <u>የማመንጨት ባለፈቃድ መብቶች እና ግዴታዎች</u>

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፲(፫)(ሀ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኤሌክትሪክ የማመንጨት ባለፈቃድ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል:-

ሀ) በፈቃዱ ውስጥ የተገለጸውን የማመንጫ ተቋም በፈቃዱ ውስጥ ከተገለጸው ማስተላለፊያ ወይም የአቅርቦት ኔትወርክ ጋር በማገናኘት ኤሌክትሪክ የመሸጥ፤

ለ) በፈቃዱ ውስጥ በተመለከተው መሠረት በዚህ ደንብ እና ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ መሠረት በአካባቢ ወይንም በዓለም አቀፍ የገበያ ትስስር በወቅታዊ የገበያ ዋጋ ኤሌክትሪክ የመሸጥ፤

ሐ) ባለስልጣኑ ባፀደቀው የኃይል ግዥ ስምምነት ላይ የተመለከተውን ክፍያ የማስከፈል፤

መ) በኢንቨስትመንት አዋጁና ሌሎች አግባብነት ባላቸው የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ከማናቸውም የኢነርጂ ምንጮች ኤሌክትሪክ የማመንጨት፤እና

ሠ) አግባብ ባለው አካል በፀደቀ ታሪፍ ወይም ባለስልጣኑ በቅድሚያ ባፀደቀው የኃይል ግዥ ስምምነት መሠረት ለማስተላለፍ ወይም ለማከፋፈል እና ለመሸጥ ባለፈቃዱ ኤሌክትሪክ የማቅረብና ክፍያ የመሰብሰብ፡፡



10/ provide appropriate training for its employees;

11/ collect revenue in accordance with the power purchase agreement and tariffs approved by the appropriate organ;

12/ comply with all notices issued by the Authority; and

13/ surrender the revoked license to the Authority within one month time.

23. **<u>Rights and Obligations of Generation Licensee</u>**

1/ Without prejudice to article 10 (3)(a) of the proclamation, a generation licensee shall have the following rights:

a) connect the generating plant stated in the license and sell electricity to the transmission system or supply network stated in the license;

b) as stated in the license and in accordance with this Regulation and directive to be issued, sell electricity in spot markets in Regional and International market network;

c) charge the rates as set out in a power purchase agreement approved by the Authority;

d) generate electricity from any energy sources in accordance with the investment proclamation and other relevant laws; and

e) supply electricity to transmission or distribution and sale licensee on the basis of tariff approved by appropriate organ or power purchase agreement pre-approved by the Authority and collect revenue.

፪/ የማመንጨት ባለፈቃዱ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል:-

ሀ) በፈቃዱ ውስጥ በተገለፀው ጊዜ እና ቅድመ ሁኔታዎች መሠረት ሥራ የመጀመር፤

ለ) ለማስተላለፊያ ግሪዱ ወይም በፈቃዱ ውስጥ ለተገለጸው የአቅርቦት ኔትወርክ ጥራቱን የጠበቀ ኤሌክትሪክ የማቅረብ፤

ሐ) በፈቃዱ ላይ ለተገለጸው አካል ብቻ ኤሌክትሪክ የመሸጥ፤

መ) ከማስተላለፊያ ግሪድ ጋር የማገናኘት ቴክኒካል ሁኔታዎችን ወይም በፈቃዱ ውስጥ የተገለጸውን የአቅርቦት ኔትወርክ ወይም በዚህ ደንብ እና ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ የተገለጹትን ሁኔታዎች የማክበር፤

ሠ) በፈቃዱ መሠረት የሚያከናውናቸው ተግባራት በአካባቢው ላይ ስላላቸው ተጽዕኖ ተገቢውን ጥንቃቄ የመውሰድ፤

ረ) በአገልግሎት ክፍያ ደንቡ መሠረት ፈቃዱን ለማስተዳደር የተወሰነውን ክፍያ የመክፈል፤

ሰ) ባለሥልጣኑ በፈቃዱ ላይ የሚያካትታቸውን ሌሎች ግዴታዎች የመፈጸም፡፡

ሸ) በማስተላለፍ ወይም በማከፋፈል እና በመሸጥ በባለፈቃዱ ጥያቄ መሠረት ኤሌክትሪክ የማመንጨትና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ተጨማሪ አገልግሎቶችን የማቅረብ፤

ቀ) የማመንጫ ተቋሙን ብቃትና አስተማማኝነት ማረጋገጥና የሕዝቡን እና የሠራተኞቹን ደህንነት የመጠበቅ፤ እና

በ) አግባብነት ያላቸውን የግሪድ እና የአፈጻጸም ኮዶችን የማክበርና ከባለሥልጣኑ ጋር ስምምነት በተገባው መሠረት ተገቢ በሆነ ጊዜ ውስጥ በግሪድ እና በአፈጻጸም ኮዶች የተቀመጡትን ግቦች የማሳካት፡፡

2/ The generation licensee shall have the following obligations:

a) start activity within the time set and pre-conditions specified in the license;

b) provide a quality electricity for the transmission grid or supply network;

c) sell electricity only to the entity set out in its license;

d) comply with the technical condition of connection to the transmission grid or supply network stated in the license or conditions specified under this Regulation and directive to be issued;

e) take appropriate measure on environmental effects of its activities under the license;

f) comply with this Regulation and the standards, conditions and codes applying to the license;

g) comply with other obligation that the Authority may set out in the license.

h) generate electricity and provide other important ancillary services based on the demand of the transmission or distribution and sale licensee;

i) maintain efficiency and reliability of the generation plant; and protect the public and employee safety; and

j) comply with the relevant grid and performance codes to achieve the targets contained in the grid and performance codes with time lines as may be set in agreement with the Authority.

**፳፬. የማስተላለፍ ባለፈቃድ መብቶች እና ግዴታዎች**

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፲(፫)(ሀ) የተደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ፣ የማስተላለፍ ባለፈቃድ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል:-

ሀ) በፈቃዱ ውስጥ የተገለጸውን የማስተላለፍ ግሪድ የመስራት፣ በፈቃዱ ውስጥ ተገልጸ ከሆነም የማስተላለፊያ ግሪዱን ከሌላ የማስተላለፊያ ግሪድ፣ የማከፋፈያ ኔትወርክ ወይም በፈቃዱ ውስጥ ከተገለጸ ማናቸውም የማስተላለፍ ቮልቴጅ ሽያጭ ቦታ ጋር የማገናኘት፤

ለ) በፈቃድ ክልሉ ውስጥ ኤሌክትሪክ የማስተላለፍ፣

ሐ) አግባብ ባለው አካል በፀደቀ የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ ታሪፍ መሠረት ለማከፋፈል እና ለመሸጥ ባለፈቃዱ ኤሌክትሪክ የማስተላለፍ፤

መ) አዋጪ የሆነ እና የሀገር ውስጥ አቅርቦቱን የማያስናክል ሆኖ ሲገኝ በአዋጁ አንቀጽ ፲፬ (፪) መሠረት ወጪና ገቢ የኃይል ሽያጭና ግዥ ሥራ ላይ አስቀድሞ በሚፈረም የኃይል ግዥ ስምምነት መሠረት ወይም በወቅታዊ የኃይል ገበያ የመሳተፍ፤

ሠ) የተገናኘውን የኤሌክትሪክ ሥርዓት ዘላቂነት፣ ደህንነት እና አስተማማኝነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ ተጨማሪ አገልግሎቶችን እንዲያቀርብለት የማመንጫ ባለፈቃዱን የመጠየቅ እና ግዥ የመፈጸም፡፡

፪/ የማስተላለፍ ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል:-

ሀ) በቂ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አስተማማኝ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ኤሌክትሪክ ማስተላለፉን ለማረጋገጥ የማስተላለፊያ ግሪዱን የማስራት፣ የመንከባከብ፣ የመጠገን እና የመጠበቅ፤

**24. Rights and Obligations of Transmission Licensee**

1/ Without prejudice to article 10 (3) (a) of the proclamation of the proclamation, the transmission licensee shall have the following rights:

a) to operate the transmission grid stated in the license; and if stated in the license, to connect the transmission grid to another transmission grid, distribution network or any transmission voltage selling point stated in the license.

b) to transmit electricity within the license area.

c) to transfer electricity to the distribution and sale licensee at transmission tariff approved by the appropriate authority; and

d) in accordance with Article 14 (2) of the Proclamation, participate in cross boarder import or export of electricity with pre signed power purchase agreement or at the spot market where feasible and do not compromise on national demand;

e) to request the generation licensee to provide necessary ancillary services and purchase such services to secure the sustainability, safety and reliability of the interconnected system.

2/ The transmission licensee shall have the following obligations:

a) operate, maintain, repair and protect its transmission grid to ensure the adequate, economic, reliable and safe transmission of electricity;

ለ) ቴክኒካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች እስከፈቀዱ ድረስ ግሪዱ የኔትወርክ አገልግሎት ለመስጠት በበቂ አቅሙ የሚሠራ መሆኑን የማረጋገጥ፤

ሐ) በዚህ ደንብ እና ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ መሠረት ተግባራዊ የሚሆኑ ደረጃዎችን፣ ሁኔታዎችን እና ኮዶችን የማክበር፤

መ) እንደአግባቡ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ከተገናኘው የሌሎች ሀገራት የማስተላለፊያ ግሪድ ጋር በመተባበር የብሔራዊ ግሪዱን ሥራ ማከናወን፤

ሠ) የማስተላለፍ ኔትወርኩ ኢኮኖሚያዊ ሆኖ ብቃት፣ አስተማማኝነት እና ዘላቂነት ኖሮት የሕዝብን እና የሠራተኞቹን ምቾት እንዲያረጋግጥ የመጠገን እና የማልማት፤

ረ) የኤሌክትሪክ ፍላጎትን አስተማማኝ እና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መልክ ለማሟላት የሚያስችል የኃይል ማመንጫ ተቋማት ጠቋሚ እቅድ የማዘጋጀት፤

ሰ) በዕቅድ ላይ ተመስርቶ የማስተላለፊያ ኔትወርኩን አቅም ከፍላጎት ጋር በማጣጣም ለአስተማማኝ አገልግሎት ዝግጁ የማድረግ፤

ሸ) አግባብነት ያላቸውን የግሪድ እና የአፈጻጸም ኮዶችን የማክበርና ከባለሥልጣኑ ጋር በስምምነት በተወሰነው ተገቢ በሆነ ጊዜ ውስጥ ግቦችን የማሳካት፤ እና

ቀ) በዕቅድ ላይ ተመሥርቶ አዲስ የኃይል ማመንጫ ተቋማትን እና ወጣ ያለ የማከፋፈያ ኔትወርክን ለማገናኘት በወቅቱ ያለውን ኔትወርክ የማጠናከር ወይም ሽፋኑን የማስፋት፡፡

b) ensure, as far as technically and economically practicable, that the transmission grid is operated with enough capacity to provide network services;

c) comply with standards, conditions and codes applying to the licensee according to this Regulation and as well as directive to be issued to implement this regulation;

d) operate the national grid, in coordination with, where appropriate, transmission grids of other countries to which it is connected directly or indirectly.

e) maintain and develop the transmission network to make it economical and thereby ensure its efficiency, reliability and sustainability; and safe for public and employees;

f) prepare power plant indicative plan in order to meet the demand of electricity at an economically justified level of reliability;

g) based on plan, make compatible the capacity of transmission network with that of the demand and make ready for reliable service provision;

h) comply with the relevant Grid or Performance Codes and achieve the targets within the time lines as may be set by the Authority; and

i) plan for reinforcing and expanding the transmission network in order to augment new generation facilities and pockets of demand at the margin of the network.

## ፳፭. የማከፋፈል እና የመሸጥ ባለፈቃድ መብቶችና ግዴታዎች

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፲(፫)(ሀ) የተደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ የማከፋፈል እና የመሸጥ ባለፈቃዱ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል:-

ሀ) በብሔራዊ ግሪድ ውስጥ በተሰጠ የፈቃድ ክልል ኤሌክትሪክ የማከፋፈል እና የመሸጥ የብቻ ፈቃድ መብት፡

ለ) ከብሔራዊ ግሪድና ከየብቻ የፈቃድ ክልል ውጭ ላሉ አገልግሎት ፈላጊዎች ኤሌክትሪክ የማከፋፈልና የመሸጥ የብቻ ያልሆነ ፈቃድ መብት፡

ሐ) ከኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ደንበኞች የኤሌክትሪክ አቅርቦትና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን የአገልግሎት ክፍያዎች አግባብ ባለው አካል በፀደቀ ታሪፍ መሠረት የመሰብሰብ፡

መ) በዚህ ደንብ እና ይህን ደንብ ለማስፈፀም በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት ከማመንጨት ወይም ከማስተላለፍ ባለፈቃድ ኤሌክትሪክ የመግዛት፡

ሠ) ደንበኛው በአዋጁና በውለታው መሠረት ኃይል ለማቋረጥ የሚያበቁ ግዴታዎቹን ሲጥስና/ወይንም ከውል ውጭ አገልግሎቱን ሲጠቀም ኃይል የማቋረጥ፡

ረ) አዋጪና የሃገር ውስጥ አቅርቦቱን የማያሰናክል ሆኖ ሲያገኘው አግባብ ባለው ፈቃድ ወጪና ገቢ የኃይል ግዥና ሽያጭ ሥራ ላይ የመሳተፍ፡ እና

ሰ/ የማከፋፈል እና የመሸጥ የብቻ ፈቃድ ሲሆን በፈቃድ ክልሉ ውስጥ የአቅርቦት ኔትወርኩን ተጠቅሞ ኤሌክትሪክ የማቅረብ፡፡

፪/ የአገልግሎት ጠያቂው ይዞታ ከባለፈቃዱ የማከፋፈል እና የመሸጥ ፈቃድ ክልል ውጭ ከሆነ ባለፈቃዱ የአቅርቦት ኔትወርኩን ለብቻ እስካልሆነው ፈቃድ ክልል ድረስ በመውሰድ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለጠያቂው መስጠት ይችላል፡፡

## 25. Rights and Obligations of Distribution and Sale Licensee

1/ Without prejudice to article 10 (3)(a) of the proclamation, the distribution and sale licensee shall have the following rights:

a) distribute and sale electricity with an exclusive right within its license area in the National Grid;

b) distribute and sale electricity without having exclusive right to the demand outside exclusive license area in the National Grid;

c) collect fees from customers for the power supplied to them and other related services provided on the bases of tariff approved by the appropriate organ;

d) purchase electricity from generation or transmission licensee according to this Regulation and Directive to be implement this regulation;

e) disconnect power, whenever the customer violates his obligation specified in the Proclamation and/or the contractual agreement;

f) participate in import or export of electricity in accordance with the provisions of the appropriate license, if viable and do not compromise supply to the national demand; and

g) to supply electricity by using the supply network within the license area when the license is an, exclusive distribution and sale license.

2/ A licensee may supply electricity to the applicant by connecting the network up to the non-exclusive license area, if applicants premises are outside of the licensee's distribution and sale area.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች እስከተሟሉ ድረስ ብቻ ነው:-

ሀ) የአገልግሎት ጠያቂው ይዞታ በሌላ የማከፋፈል እና የመሸጥ ባለፈቃድ የማከፋፈል እና የመሸጥ ክልል ውስጥ ካልሆነ፣

ለ) በሌላ የማከፋፈል እና የመሸጥ ባለፈቃድ ክልል ከሆነ ቴክኒካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች አንጻር ተግባራዊ ለማድረግ ለሌላኛው ማከፋፈል እና መሸጥ ባለፈቃዱ ስለማይቻል ለጠያቂው ኤሌክትሪክ ለማቅረብ የማይችል መሆኑ ከታወቀ፣ ወይም የማከፋፈል እና የመሸጥ ባለፈቃዱን ለማገናኘት እና ለማቅረብ የሚስማማ ከሆነ፣ እና

ሐ) ኃይል የማቅረብ ባለፈቃዱ በራሱ የማከፋፈል እና የመሸጥ ክልል ውስጥ ያለበትን ግዴታዎቹን ለማሟላት የማይጎዳው እስከሆነ ድረስ ብቻ ነው፡፡

፬/ የማከፋፈል እና የመሸጥ ባለፈቃዱ የአዋጁ አንቀጽ ፲ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ግዴታዎች አለበት:-

ሀ) በውሉ መሠረት ለደንበኞች ኤሌክትሪክ የማቅረብ፤

ለ) በፈቃዱ ክልል ውስጥ ለአዲስ ኃይል የማገናኘት ጥያቄ ፈጣን ምላሽ የመስጠት፤

ሐ) የታቀደ የኤሌክትሪክ ማቋረጥን ከ፸፪ (ከሰባ ሁለት) ሰዓታት በፊት ለደንበኞች የማሳወቅ፤

መ) ለደንበኞች ስለኤሌክትሪክ አጠቃቀም አስፈላጊ የሆነ መመሪያ የመስጠት፤

ሠ) ብቁ፣ አስተማማኝ እንዲሁም የኅብረተሰቡን፣ የሠራተኞችን እና የደንበኞችን ደህንነት በሚያረጋግጥ ሁኔታ የማከፋፈያ ሥርዓቱን የማልማት እና የመንከባከብ፤

3/ Sub-Article (2) of this Article shall apply only if:

a) the premises of the applicant is not within another distribution and sale licensee area;

b) the applicant premises is in another distribution and sale licensee's area and the other distribution and sale licensee claims that it is not technically and economically practicable for it to connect and supply electricity to the applicant; or the distribution and sale licensee agrees to connect and supply; and

c) the supply of electricity is not likely to impair the licensee's capacity to fulfill its obligation to connect and supply in its own distribution and sale area.

4/ without prejudice to article 10 of the proclamation the distribution and sale licensee shall, have the following obligations:

a) supply electricity to customers according to the agreement;

b) respond promptly to connection demand of new customers within its license area;

c) notify customers before 72 (seventy-two) hours in advance of planned outages;

d) provide customers with the necessary guidance on the use of electricity;

e) develop and maintain the distribution system to ensure its efficiency and reliability; and safety of public, employees and customers;

ረ) አግባብነት ያላቸውን የግሪድ እና የአፈጻጸም ኮዶችን የማክበርና ከባለሥልጣኑ ጋር በተደረሰው ስምምነት መሠረት ተገቢ በሆነ ጊዜ ውስጥ በኮዶችና በአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃዎች ላይ የተቀመጡትን ግቦችን የማሳካት፣

ሰ) ለደንበኞች አቤቱታ አፋጣኝ ምላሽ የመስጠት፣

ሸ) የደንበኞችን አቤቱታዎች መዝግቦ የመያዝ እና በሦስተኛ አካል ሊደረግ ለሚችል ምርመራ ዝግጁ የማድረግ፣

ቀ) የደንበኞች አቤቱታ የሚሰማበትንና የሚፈታበትን መድረክ የማቋቋም፣

በ) በእቅድ ላይ ተመስርቶ የማከፋፈያ ኔትወርኩን አቅም ከፍላጎት ጋር በማጣጣም ለአስተማማኝ አገልግሎት ዝግጁ የማድረግ፣

ተ) በዕቅድ ላይ ተመሥርቶ አዲስ የኃይል ማመንጫ ተቋማትን ለማገናኘት በወቅቱ ያለውን ኔትወርክ የማጠናከር ወይም ሽፋኑን የማስፋት፣

ቸ) ኢኮኖሚያዊ ብቃት እንደሚያመጡ የታመነባቸውን የደንበኞች የኃይል አጠቃቀም ማሻሻያ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ፕሮግራሞች እንዲተገበሩ የማድረግ እና ለፕሮግራሞቹ አግባብ የሆነ የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት በቅድሚያ በባለሥልጣኑ ተቀባይነት የማግኘት፣

ኀ) በትክክለኛ የኤሌክትሪክ ፍጆታ ንባቦች በመመስረት ግልጽ እና ትክክለኛ ደረሰኝ የመስጠት፤ እና

ነ) ለደንበኞች አመቺ የሆነ የቅድመ ክፍያ ቆጣሪ አስተዳደርንና የክፍያ ዘዴን የመተግበር፡፡

f) achieve the targets contained in the Grid Code and service performance standard agreements reached with the Authority within a reasonable time specified in the contract;

g) respond promptly to customer complaint;

h) record customers complaints and prepare them for inspection by a third party;

i) establish a forum for hearing and resolution of complaints of customers;

j) plan for reliable service by upgrading the distribution network capacity that commensurate with demand;

k) plan for network reinforcement or expansion in anticipation of connection with new power generation facilities;

l) implement energy efficiency and conservation programs proven to be economically beneficial, and obtain prior approval of the Authority to secure financial support for such programs;

m) issue correct and clear receipts based on accurate meter reading; and

n) facilitate to customers appropriate pre-payment meter management and billing system.

፭/ ቦታው በባለፈቃዱ የማከፋፈል እና የመሸጥ ክልል ውስጥ ከሆነና የቦታው ባለይዞታ ለቦታው የኤሌክሪትክ አገልግሎት እንዲሰጠው ከጠየቀ ባለፈቃዱ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

፮/ ባለፈቃዱ የደንበኛውን ማመልከቻ በተቀበለ በ፪ (በሁለት) ወር ውስጥ የኤሌክትሪክ አገልግሎት መስጠት አለበት፤ ሆኖም በወቅቱ አገልግሎቱን ለመስጠት የማያስችለው አሳማኝ ሁኔታ ካለ ለደንበኛው በጽሁፍ መግለጽ ይኖርበታል፡፡

፯/ ባለፈቃዱ ለአገልግሎት ጠያቂው የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለማቅረብ ሲወስን ከአገልግሎት ጠያቂው ጋር ውል መፈጸም አለበት፡፡

፰/ ባለፈቃዱ ለደንበኞቹ በቂ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አስተማማኝ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ኤሌክትሪክ ማገናኘት እና ማቅረብ በሚያስችል ሁኔታ የአቅርቦት ኔትወርኩን መገንባት፣ ሥራውን ማከሄድ፣ መጠገን እና መጠበቅ አለበት፡፡

፱/ ብቃት ያለው የኤሌክትሪክ አቅርቦትን ለማረጋገጥ እንዲቻል ባለፈቃዱ ቴክኒካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች እስከፈቀዱ ድረስ የፍላጎት እና የአቅርቦት አማራጮችን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

፲/ ባለፈቃዱ ለዚህ ደንብ ተፈጻሚ የሚሆኑ ደረጃዎች፣ ፕሮቶኮሎች፣ ኮዶች እና ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚወጣ መመሪያን የማክበር እና በራሱ ኔትወርክ ሥር ያለውን የአቅርቦት ኔትወርክ የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት፡፡

**፳፮. የአስመጪና ላኪ ባለፈቃድ መብቶችና ግዴታዎች**

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፲(፫)(ሐ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አስመጪ እና ላኪ ባለፈቃዱ የሚከተሉት መብቶች አሉት፡-

5/ The licensee shall have an obligation to supply electricity to the possessor of a premise, if the possessor applies for the provision of electricity service to the premise and such premise is within the licensee's distribution and sale area.

6/ The licensee shall supply electricity within 2 (two) months of receiving the application from the customer; provided, however, where there is sufficient reasons for not supplying it shall notify the customer in writing.

7/ When the licensee decides to supply electricity to the applicant it shall conclude a contract with the applicant.

8/ A licensee shall construct, operate, maintain and protect its supply network in a way that ensure the adequate, economic, reliable and safe connection and supply electricity to its customers.

9/ A licensee shall consider both demand side and supply side options to provide, as far as technically and economically practicable to ensure efficient supply of electricity.

10/ A licensee shall comply with all standards, protocols and codes applying to the licensee under this regulation and well as directive to be issued to implement this regulation and have the responsibility of network control of its supply network.

**26. Right and Obligation of Import and Export Licensee**

1/ Without prejudice to article 10 (3) (c) of the proclamation import and export Licensee shall have the following rights:

ሀ) በፈቃዱ ላይ በተገለጸው የፈቃድ አግባብና ሁኔታ መሠረት እንዲሁም እንደአግባቡ በሚደረስ የማስተላለፊያ ስምምነት መሠረት የኤሌክትሪክ ኃይልን ወደሃገር ውስጥ ለማስገባት ወይንም ወደውጭ ሃገር ለመላክ ብሔራዊ ግሪዱን በመጠቀም የማስተላለፍ፣

ለ) በፈቃዱ ላይ በተገለጸው የፈቃድ አግባብና እንደአግባቡ በሚደረስ የማስተላለፍ ስምምነት መሠረት በብሔራዊ ግሪዱ ውስጥ ያለአድልኦ የመገልገል፡፡

፪/ አስመጪ እና ላኪ ባለፈቃዱ የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት:-

ሀ) እንደአግባብነቱ አሰራሩን ከብሔራዊ የማከፋፈያና የማስተላለፊያ ግሪድ ኮድ ጋር የተጣጣመ የማድረግ፣

ለ) የፀደቀ ሪጅናል ግሪድ ኮድ ባለበት ሁኔታ አሰራሩን ከሪጅናል ግሪድ ኮድ ጋር የማጣጣም፡፡

፳፯. <u>የደንበኛ መብቶችና እና ግዴታዎች</u>

፩/ ደንበኛ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል:-

ሀ) ከባለፈቃዱ አስተማማኝ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የኤሌክትሪክ አገልግሎት የማግኘት፣

ለ) እንደየአግባቡ ከኤሌክትሪክ አገልግሎት ጋር በተያያዘ ማናቸውም አቤቱታ በባለሥልጣኑ በሚወጣ የአሰራር ሥርዓት መሠረት ለባለፈቃዱ ወይም ለባለሥልጣኑ የማቅረብ፣ እና

ሐ) ደረጃውን ባልጠበቀ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ምክንያት በዕቃዎች እና መገልገያዎች ላይ ለሚደርስ ማናቸውም ጉዳት ተመጣጣኝ ካሣ በወቅቱ የማግኘት፡፡

a) to transmit import or export electricity by using the national Grid in accordance with the terms and conditions specified in the License and as per the transmission service agreements as may be applicable while importing and exporting electricity;

b) to have an access to national transmission grid on non discriminatory bases in accordance with the terms and conditions specified in the License and as per the transmission service agreements as may be applicable.

2/ The import or export licensee shall have the following obligations:

a) To comply with national distribution and transmission grid code as may be applicable;

b) To comply with the regional Grid code, where there is an approved regional Grid code.

27. **<u>Rights and Obligations of Customer</u>**

1/ Customer shall have the following rights:

a) get reliable, economical and safe electricity services from licensees;

b) submit any complain related to electricity services, as appropriate, to the licensee or the Authority in accordance with procedures to be issued by the Authority; and

c) obtain timely and proportional compensation for any damage on equipments and appliance caused by services not in line with the service standard.

፪/ ደንበኛ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል:-

ሀ) ስለኤሌክትሪክ አጠቃቀም የወጡ ማስታወቂያዎችንና ትዕዛዞችን የማክበር፣

ለ) በደንበኛው ይዞታ ውስጥ የኤሌክትሪክ ሥራዎች ሲከናወኑ የመተባበር፣

ሐ) ኤሌክትሪክን በውሉ ውስጥ ከተገለጸው አገልግሎት ውጭ ያለመጠቀም፣

መ) ለተጠቀመበት ኤሌክትሪክ ክፍያ የመፈጸም፣

ሠ) ከኤሌክትሪክ አቅርቦት ጋር በተያያዘ ማናቸውም ያልተለመደ ሁኔታ ሲያጋጥም ለባለፈቃዱ በፍጥነት የማሳወቅ፣ እና

ረ) በባለሥልጣኑ የፀደቀውንና በባለፈቃዱ የወጣውን አግባብነት ያለውን የደንበኞች ቻርተር ድንጋጌ የማክበር፡፡

**፳፰. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው መብቶች እና ግዴታዎች**

፩/ ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል:-

ሀ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጠበት አግባብ የተፈቀዱ የኤሌክትሪክ ሥራዎችን በሀገሪቱ ውስጥ የማከናወን፣

ለ) በዚህ ደንብ በተገለጸው ሁኔታ ካመለከተ እና አስፈላጊ መስፈርቶችን ካሟላ በ፲፭ (በአሥራ አምስት) ቀናት ውስጥ እንደአግባቡ፣ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እድሳት ወይም፣ ምትክ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የማግኘት፡፡

፪/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ሰው የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል:-

ሀ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኘበትን ተግባር በከፍተኛ ጥንቃቄና ደረጃውን በጠበቀ የሥራ አፈጻጸም የማከናወን፣

2/ Customer shall have the following obligations:

a) comply with notices and instructions on the use of electricity;

b) cooperate for the electrical works to be performed within the premises of the customer;

c) not to use electricity for the services other than specified in the contract;

d) pay for the electricity consumed;

e) promptly notify the licensee of any irregularities of electricity supply; and

f) comply with the relevant provision of customers' charter issued by the licensee and approved by the Authority.

**28. Rights and Obligations of Holder of Certificate of Competency**

1/ Any holder of certificate of competency shall have the following rights:

a) to undertake the permitted electrical work activities within the country in accordance with certificate issued.

b) within 15 (fifteen) days from the date of fulfilling the necessary requirements specified by this regulation get or renewal or replacement of certificate of competency;

2/ Any holder of certificate of competency shall have the following obligations:

a) undertake its certified activities on a prudent operating practice and with acceptable standards;

ለ) በባለሥልጣኑ የወጣ የሥነ ምግባር ኮድን የማክበር፣

ሐ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ለሌላ ማንኛውም ሰው በማንኛውም መልኩ አሳልፎ ያለመስጠት፣

መ) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ ከተሰረዘ ወዲያውኑ ለባለስልጣኑ የመመለስ፡፡

## ክፍል አራት
## ስለኤሌክትሪክ ታሪፍ እና ስለግሪድ አጠቃቀም

### ንኡስ ክፍል አንድ
### ስለኤሌክትሪክ ታሪፍ

**፳፱. አጠቃላይ መርሆዎች**

ባለሥልጣኑ የግሪድና ተያያዥነት ያለውን ታሪፍ ለመገምገም እና የውሳኔ ሀሳብ ለማቅረብ ወይም ከግሪድ ውጭ ያለውን ታሪፍ ለማፅደቅ በሚከተሉት መርሆዎች ይመራል:-

፩/ ኤሌክትሪክ የማመንጨት፣ የማስተላለፍ፣ የማከፋፈል እና የመሸጥ ተግባራት በዘርፉ የንግድ መርሆዎች እና የላቀ አሰራር መሠረት መመራታቸውን፣

፪/ እንደአግባቡ ውድድር ማበረታታቱን፣ የሀብት አጠቃቀሙ ኢኮኖሚያዊ መሆኑን፣ የአፈጻጸም ብቃቱ፣ ግልጽነቱ፣ የኃይል አቅርቦት ሥርዓቱ የተቀናጀ መሆኑን እና የኤሌክትሪክ ዘርፉ መዋዕለ ንዋይ መሳብ መቻሉን፣

፫/ የደንበኞችን ፍላጎት ማሟላቱን እና አግባብነት ባለው ደንብ መሠረት የኤሌክትሪክ ወጪው መሸፈኑን፣

፬/ ከአንድ ዓመት በላይ ጸንቶ የሚቆይ ታሪፍ መሆኑን፣

፭/ ከታዳሽ የኃይል ምንጮች እና የሚባክን የሙቀት ኃይልን ተጠቅሞ ኤሌክትሪክ ማመንጨትን ማበረታታቱን፣

፮/ በድጎማ፣ በጎንዮሽ ድጎማ ወይም በስጦታ የተሸፈነ ወጪን በንግድ ሥራው ወጪ ውስጥ ያለመካተታቸውን፣ እና

፯/ በተቻለ መጠን የታሪፍ ክለሳው የዋጋ መረጋጋትን የሚያረጋግጥና ለመተግበር የሚያመች መሆኑን፡፡

b) comply with the code of conduct issued by the Authority;

c) not transfer the certificate of competency to any other person for any purpose;

d) return immediately the revoked licence to the Authority.

## PART FOUR
## ELECTRICITY TARIFF AND GRID ACCESS

### SUB-SECTION ONE
### ELECTRICITY TARIFF

**29. General Principles**

In reviewing and recommending grid related tariff or approving off-grid tariff the Authority shall be guided by the following principles:

1/ the generation, transmission, distribution and sale of electricity are conducted on the basis of commercial principles and best practice of the sector;

2/ the factors which would encourage competition, efficiency, economical use of the resource, efficiency in performance, transparency, accommodating the needs of system integrity and attract investment to the electricity sector, as appropriate;

3/ safeguarding customers interest and at the same time recover cost of electricity as per the relevant Regulation;

4/ application of tariff principles for more than a year;

5/ the promotion of co-generation and generation of electricity from renewable energy sources;

6/ costs covered by subsidy, cross-subsidy or grant shall not be reflected in the costs of business operations; and

7/ tariff adjustments shall, to the extent possible, ensure price stability and simplicity of administration.

**፴. ስለታሪፍ ግምገማ፣ የውሳኔ ሀሳብ እና ማፀደቅ**

፩/ ኤሌክትሪክ ከማመንጨት፣ ከማስተላለፍ፣ ከማከፋፈል እና ከመሸጥ ጋር በተያየዘ የግሪድ ታሪፍ ሲገመገም እና የውሳኔ ሀሳብ ሲቀርብ ወይም ከግሪድ ውጭ ያለ ታሪፍ ሲፀድቅ የሚከተሉትን እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሁኔታዎች ከግንዛቤ ሊያስገባ ይችላል:-

ሀ) የነዳጅ ወጪን፣

ለ) የኃይል ግዥ ወጪን፣

ሐ) የዋጋ ግሽበት ምጣኔን፣ እና

መ) የውጭ ምንዛሪ መዋዠቅን፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ ከግሪዱ ጋር ተያያዥነት ያለውን ታሪፍ ሲገመግም እና የውሳኔ ሀሳብ ሲያቀርብ ወይም ከግሪድ ውጭ ያለውን ታሪፍ ሲያፀድቅ በታሪፍ መመሪያው በተገለጸው መሠረት አስፈላጊ ናቸው ብሎ የሚያምንባቸውን መረጃዎች እንዲያቀርብ ባለፈቃዱን ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ ከግሪዱ ጋር ተያያዥነት ያለውን ታሪፍ ሲገመግም እና የውሳኔ ሀሳብ ሲያቀርብ ወይም ከግሪድ ውጭ ያለን ታሪፍ ሲያፀድቅ ለማንኛውም የኤሌክትሪክ ደንበኛ ከዚህ ቀጥሎ ከተመለከቱት ውጭ አላስፈላጊ ልዩነት ማድረግ የለበትም:-

ሀ) የደንበኞች ሎድ ፋክተር፣ ፓወር ፋክተር፣ ቮልቴጅ፣

ለ) በማንኛውም የተወሰነ ጊዜ ውስጥ ያለን የኤሌክትሪክ ፍጆታ፣

ሐ) የማናቸውም ስፍራ መልክዓ ምድራዊ የቦታ አቀማመጥ፣ የአቅርቦቱን ባህሪ እና የተፈለገበት ተግባር፡፡

**፴፩. ስለታሪፍ ግምገማ፣ የውሳኔ ሀሳብ እና የማፀደቅ ሥነ-ሥርዓት**

፩ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፱ መሠረት ከግሪዱ ጋር ተያያዥነት ያለውን ታሪፍ ለግምገማ እና ለውሳኔ ሀሳብ ወይም ከግሪድ ውጭ የሆነን ታሪፍ ለማፀደቅ ባለፈቃዱ ማመልከቻውን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

**30. Tariff Review, Recommendation and Approval**

1/ In reviewing and recommending grid related tariff or approving off-grid tariff in relation to generation, transmission, distribution and sale of electricity, the following and other appropriate factors may be considered:

a) cost of fuel;

b) cost of power purchase;

c) the rate of inflation or deflation; and

d) foreign currency fluctuation.

2/ In reviewing and recommending grid related tariff or approving off-grid tariff the Authority may require a licensee to furnish separate details, as may be specified, in the tariff directive.

3/ The Authority shall not, while reviewing and recommending grid related tariff or approving off-grid tariff, show undue preference to any customer of electricity; except on the bases of the following:

a) customers load factor, power factor, voltage;

b) total consumption of electricity during any specified period; or

c) the geographical location, the nature of supply and the purpose for which the supply is required.

**31. Procedure for Tariff Review, Recommendation and Approval**

1/ The licensee shall submit application to the Authority for reviewing and recommending grid related tariff or approval of off-grid tariff under Article 29 of this Regulation.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ባለሥልጣኑ ማመልከቻውን በተቀበለ በ፩፻፳ (በአንድ መቶ ሃያ) ቀናት ውስጥ እና ከሕዝብ የተቀበለውን አስተያየት እና ተቃውሞ ከግምት ውስጥ በማስገባት አስፈላጊ ማስተካከያዎችን በማድረግ ከግሪድ ውጭ ታሪፍን ያፀድቃል ወይም ምክንያቱን በመመዝገብ ማመልከቻውን ውድቅ ያደርጋል፡ ሆኖም ማመልከቻውን ውድቅ ከማድረጉ በፊት የባለፈቃዱ ሀሳብ እንዲሰማ እድል መሰጠት አለበት፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ ከግሪዱ ጋር ተያያዥነት ያለውን ታሪፍ የውሳኔ ሀሳብ ለማፀደቅ አግባብነት ላለው የመንግሥት አካል ማቅረብ አለበት፡፡

፬/ ባለሥልጣኑ ከግሪዱ ጋር ተያያዥነት ያለውን ታሪፍ ወይም ከግሪድ ውጭ ያለው ታሪፍ በፀደቀ በ፯ (በሰባት) ቀናት ውስጥ የፀደቀውን ታሪፍ ቅጅ ለሚመለከተው ባለፈቃድ መላክ አለበት፡፡

፭/ ባለፈቃዱ የፀደቀውን ታሪፍ በኅብረተሰቡ ዘንድ በቂ ግንዛቤ እንዲፈጠር ሰፊ ተደራሽነት ባለው መገናኛ ብዙሃንና ሌሎች የመገናኛ መንገዶችን በመጠቀም ለሕዝብ ማስታወቅ አለበት፡፡

፮/ ባለሥልጣኑ ሁሉም ባለፈቃዶች ሊከተሉት የሚገባ የሚከተሉትን ክፍሎች ያካተተ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል:-

ሀ) ቁጥጥር የሚደረግበት መሠረታዊ ንብረት፣

ለ) የእርጅና ቅናሽ፣

ሐ) የሥራ ካፒታል፣

መ) የካፒታል ወጪ፣

ሠ) ከኢንቨስትመንት የሚገኝ ትርፍ፣

ረ) የደንበኛ ማገናኛን ጨምሮ የሥራ ማስኬጃና የጥገና ወጪ፣እና

ሰ) ሌሎች ግንኙነት ያላቸውን ወጪዎች፡፡

2/ The Authority shall, within 120 (one hundred twenty) days from receipt of an application as provided under sub-Article (1) of this Article and after considering all suggestions and objections received from the public, approve off-grid tariff with such modifications or reject the application for reasons to be recorded; provided, however, that an applicant shall be given an opportunity to be heard before rejecting his application.

3/ The Authority shall submit the recommended grid related tariff for approval to the relevant Government Organ.

4/ The Authority shall send copy of grid related tariff and off-grid tariff to the concerned licensee within seven (7) days of such approval.

5/ The licensee shall, in order to create public awareness, publicize to the public the approved tariff using mass media outlets having wide coverage and other communication media.

6/ The Authority may issue directive containing the following components about income capacity conditions to be followed by all licensees:

a) regulatory asset base;

b) depreciation;

c) working capital;

d) cost of capital;

e) return on investment;

f) operation and maintenance expenses, including customer connection costs; and

g) other related costs.

፯/ ባለፈቃዱ ባለስልጣኑ በሚያወጣው የታሪፍ ስሌት ሥርዓት መሠረት የታሪፍ ክለሳ ጥናት በየአራት ዓመቱ ማካሄድ እና የጥናት ሪፖርቱንም ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

፰/ ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) ከተቀመጠው የታሪፍ ማስተካከያ የጊዜ ገደብ ውጭ ባለፈቃዱ የታሪፍ ክለሳ ጥያቄ ስለሚያቀርብበት አግባብ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል፡፡

**፴፪. ወጥ ስለሆነ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓትና የኦዲት ሪፖርት**

፩/ ባለሥልጣኑ በሁሉም ባለፈቃዶች ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረው የታሪፍ ሥርዓትን የሚደግፍ፣ የሂሳብ አያያዝ መርሆዎችን መሠረት ያደረገ ወጥ የሆነ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ ያወጣል፡፡

፪/ ማንኛውም ባለፈቃድ የሂሳቡን ኦዲት ሪፖርት የመንግሥት በጀት ዓመት ባለቀ በ፮ (በስድስት) ወራት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

**ንዑስ ክፍል ሁለት**

**ስለግሪድ አጠቃቀም**

**፴፫. መርሆዎች**

፩/ በፈቃዱ ላይ በተገለጸው የፈቃድ ሁኔታዎች መሠረት የብሔራዊ ማስተላለፊያ ግሪዱ ለዓለም አቀፋዊ የኃይል ትስስር ክፍት ይሆናል፤ አጠቃቀሙም ግልጽና ወጪን ያገናዘበና በሚፀድቅ የማስተላለፍ ስምምነት መሠረት መሆን አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ በተደነገገው መሠረት የብሔራዊው የማስተላለፊያ መስመር አጠቃቀም በነባር ተገልጋይ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሣድር መሆን የለበትም፡፡

7/ The licensee shall conduct tariff review study every four years of interval in accordance with tariff procedure to be issued by the Authority and shall submit the study report to the Authority.

8/ The Authority shall determine by Directive for submission of tariff application by licensee other than the tariff application procedure provided under sub-article (7) of this Article.

**32. Uniform System of Accounts and Audit Report**

1/ The Authority shall issue directive on uniform system of accounting based on generally accepted accounting principles to support the tariff regulation efforts and be applied by all licensees.

2/ Any licensee shall submit audited reports of its accounts to the Authority within 6 (six) months from the end of the government's fiscal year.

**SUB-SECTION TWO**

**GRID ACCESS**

**33. Principles**

1/ Based on the conditions specified in the license, access to and use of the national transmission grid shall be open for international power trade; and its use shall be, transparent and cost-reflective, and based on transmission service agreement to be approved.

2/ Access to the national transmission grid as provided under sub-article (1) of this Article, shall not adversely affect services of the existing customers.

**፴፬. አጠቃቀምን ስለመከልከል**

፩/ ባለፈቃዱ የብሔራዊ የማስተላለፊያ ግሪዱ ትስስር ወይም አጠቃቀም በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፫ ላይ ከተደነገገው የግሪድ አጠቃቀም መርህ ጋር የሚጋጭ ከሆነ ሁኔታው እስከሚሻሻል ድረስ ትስስሩን ወይም አጠቃቀሙን መገደብ ወይም መከልከል ይችላል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በባለፈቃዱ የተወሰደው እርምጃ አግባብ መሆን አለመሆኑን በማጣራት ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## ክፍል አምስት
## ስለኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ
## ምዕራፍ አንድ
## ስለኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ኦዲት፣ ተቋራጭነት ወይም የማማከር አገልግሎት ፈቃድ እና ስለ ፈንድ

**፴፭. ስለፈቃድ ማመልከቻ አቀራረብ**

፩/ ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ኦዲት፣ ተቋራጭነት ወይም የማማከር አገልግሎቶችን ማከናወን አይችልም፡፡

፪/ ማንኛውም የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ኦዲት፣ የተቋራጭነት ወይም የማማከር ፈቃድ ማመልከቻ ለባለሥልጣኑ ሲቀርብ የሚከተሉትን መያዝ አለበት:-

ሀ) የአመልካቹን አድራሻ፣ የመታወቂያውን ኮፒ፣

ለ) እንደየአግባቡ የተቀጣሪ ሠራተኞችን የብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ፣

ሐ) እንደየአግባቡ ዲግሪ፣ ዲፕሎማ ወይም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና ቀጥታ ግንኙነት ያለው የሥራ ልምድ፣ እና

መ) ባለሥልጣኑ በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች፡፡

፫/ አመልካቹ የጠየቀው ፈቃድ ሊሰጥ የሚችል መሆን አለመሆኑን ለመመዘን እና የፈቃዱን ደረጃ ለመወሰን በአገልግሎት ክፍያ ደንቡ መሠረት የማይመለስ የማመልከቻ መመርመሪያ ክፍያ ከፈቃድ ማመልከቻ ጋር መቅረብ አለበት፡፡

**34. Refusal of Access**

1/ The licensee may refuse or prevent connection or access, until the condition are improved, when the national grid connection or access contradict with grid access principle provided under Article 33 of this Regulation.

2/ The Authority shall examine and pass decision on the reliability of the measure taken by the licensee pursuant to sub-article (1) of this Article.

## PART FIVE
## ENERGY EFFICIENCY AND CONSERVATION
## CHAPTER ONE
## LICENSING OF ENERGY EFFICIENCY AND CONSERVATION AUDIT, CONTRACTING ORCONSULTANCY SERVICE AND FUND

**35. Submission of Application for License**

1/ No person shall undertake energy efficiency and conservation audit, contracting or consultancy service without being issued a license from the Authority.

2/ Any application for energy efficiency and conservation, audit, contracting or consultancy license to be submitted to the Authority shall contain the following:

a) address of the applicant and copy of his identity card;

b) as appropriate, certificate of competence of recruited employees;

c) as appropriate, degree, diploma or certificate of competence acquired and directly relevant experience; and

d) other relevant information the Authority may determine by a directive.

3/ An application for a license shall be accompanied by a non-refundable application fee prescribed under the Service Fee Regulation for examining whether the license should be issued or not and to determine the grade of the license to be issued.

፬/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የቀረቡትን መረጃዎች ትክክለኛነት ካረጋገጠ በኋላ የአመልካቹን ብቃት ለመመዘን እና የፈቃዱን ደረጃ ለመወሰን እንደየአግባቡ የጽሁፍ ወይም የተግባር ፈተና ሊሰጥ ይችላል፡፡

፭/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተጠቀሱትን የፈቃድ ምዘና እና የደረጃ መስፈርቶችን በተመለከተ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፮/ ባለሥልጣኑ አመልካቹ የፈቃድ መስፈርቶችን ማሟላቱን ካረጋገጠ በኋላ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ፈቃዱን መስጠት አለበት፡፡

፯/ ባለሥልጣኑ በአመልካቹ የቀረበው መረጃ በቂ አይደለም ብሎ ከወሰነ ውሳኔውን ለአመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

**፴፮. ስለፈቃድ ማመልከቻ ምዝገባ የቀረበው የፈቃድ ማመልከቻ ጥያቄ**

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፭ መሠረት ተሟልቶ የቀረበ እንደሆነ ለዚሁ ተግባር በባለሥልጣኑ ቢሮ ውስጥ በተዘጋጀ የማመልከቻ መመዝገቢያ መዝገብ ላይ ወዲያውኑ እንደቅደም ተከተሉ እንዲመዘገብ ተደርጎ ለእያንዳንዱ አመልካች የምዝገባ ቀኑን እና ቁጥሩን የሚያመለክት ደረሰኝ መሰጠት አለበት፡፡

**፴፯. ፈቃድ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ እና እድሳት**

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፭ መሠረት የተሰጠ ፈቃድ፡-

ሀ) ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለ፪ (ለሁለት) ዓመታት ፀንቶ ይቆያል፤

ለ) በየሁለት ዓመቱ መታደስ አለበት፤

ሐ) ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ከማብቃቱ ከ፲፭ (ከአሥራ አምስት) ቀናት በፊት ለእድሣት መቅረብ አለበት፡፡

4/ The Authority may, as may be appropriate, give a written or practical examination to evaluate the competency of the applicant and grade of the license, following the verification of information submitted in accordance with to sub-Article (2) of this Article.

5/ The Authority may issue directive regarding evaluation and , grading requirements of the license referred under sub-article (4) of this Article.

6/ The Authority shall issue the license upon payment of the prescribed fee after verifying that an applicant has fulfilled the requirements of license.

7/ If the Authority decides that the information supplied by the applicant is inadequate, it shall, notify the decision to the applicant in writing.

**36. Registration of Application for License Request**

When the application lodged for license is complete in accordance with Article 35 of this Regulation, it shall immediately be registered in the order it is received in the application registration book maintained in the office of the Authority for such purpose and each applicant be given a receipt indicating the date and number of registration.

**37. Validity Period and Renewal of License**

1/ A license issued pursuant to Article 35 of this Regulation shall be:

a) valid for a term of 2 (two) years starting from the date of its issuance;

b) renewed every two years;

c) submitted for renewal at least 15 (fifteen) days prior to its expiry date.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሐ) መሠረት ለእድሳት ሳይቀርብ የፈቃዱ ዘመን ያበቃበት ማንኛውም ሰው የእድሳት ዘመኑ ካበቃበት በኋላ ባሉት ፺(ዘጠና) ቀናት ውስጥ ፈቃዱ እንዲታደስለት ሊያመለክት የሚችል ሲሆን ባለሥልጣኑም ፈቃዱ ካበቃበት በኋላ ላለው ለእያንዳንዱ ቀን በአገልግሎት ክፍያ ደንቡ የተመለከተውን የዘገየ እድሳት ክፍያ በማስከፈል ፈቃዱን ያድስለታል፡፡

፫/ ፈቃድ ለማሳደስ የሚፈልግ ማንኛውም ባለፈቃድ ፈቃዱ ጸንቶ በቆየበት ጊዜ ውስጥ በፈቃዱ ስላከናወነው ተግባር የተሟላ ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

፬/ ማንኛውም ፈቃድ የተሰጠው የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት ፈቃዱን ለማሳደስ ሲቀርብ የተቀጣሪ ባለሙያዎቹን የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

**፴፰. ስለምትክ ፈቃድ**

፩/ ማንኛውም ባለፈቃድ የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል ለጠፋበት ወይም ለተበላሸበት ፈቃድ ምትክ እንዲሰጠው ለባለሥልጣኑ ሊያመለክት ይችላል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ማመልከቻውን ከተቀበለ በኋላ መርምሮ በአገልግሎት ክፍያ ደንቡ የተወሰነውን በማስከፈል ምትክ ፈቃዱን መስጠት አለበት፡፡

**፴፱. ፈቃድን ስለማገድ ወይም ስለመሰረዝ**

፩/ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ የኢነርጂ ኦዲት፣ የማማከር ወይም የተቋራጭነት ፈቃድ ሊታገድ ይችላል:-

ሀ) በፈቃዱ ላይ ከተጠቀሰው ገደብ ውጭ በሥራ ላይ መሰማራት ወይም ደረጃውን ያልጠበቀ ሥራ መሥራት፤

ለ) የሰራው ሥራ መሠረታዊ የሆነ የደህንነትና የጥራት ችግር ያለበት በመሆኑ ምክንያት በተገልጋዩ ህይወት ወይም ንብረት ላይ አደጋ መፍጠር፤

2/ Any person whose license has been expired due to failure to renew pursuant to sub-article (1) (c) of this article may apply for renewal within 90 (ninety) days following the expiry date; and the Authority shall renew upon payment of delayed renewal fee specified under Service Fee Regulation.

3/ Any licensee who wants to renew his license shall produce a complete report of the activity performed on the same license year.

4/ Any juridical person wants to renew its license shall produce to the Authority a valid certificate of competence of its employees.

**38. Replacement of License**

1/ Any licensee may, upon the payment of the prescribed fee, apply to the Authority for the replacement of the license which has been lost or destroyed.

2/ The Authority, after receiving application pursuant to sub-article (1) of this Article, shall issue a replaced license upon payment of the service fee prescribed in the Service Fee Regulation.

**39. Suspension or Revocation of License**

1/ A license of energy audit, consultancy or contracting may be suspended due to one of the following reasons:

a) engaging in activity beyond authorized in the license issued by the Authority; or perform below standard;

b) causing damage on life or property of service user due to substantial safety and quality problem of the work performed;

ሐ) በዚህ ደንብ መሠረት ማቅረብ የሚጠበቅበትን ሪፖርት አሟልቶ አለማቅረብ ወይም የተሳሳተ ሪፖርት ማቅረብ ወይም አስፈላጊ ሰነዶችን በአግባቡ አለመያዝ፤

መ) የባለሥልጣኑ የቁጥጥር ሥራ እንዳይከናወን ሆን ብሎ እክል መፍጠር ወይም ማወክ፣ ወይም

ሠ) በባለስልጣኑ የተሰጠውን ፈቃድ ያለባለሥልጣኑ ስምምነት ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት፡፡

፪/ ፈቃድ የታገደበት ማንኛውም ሰው በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማስተካከያ እርምጃ ያልወሰደ እንደሆነ ወይም በሁለት ዓመት ውስጥ እገዳን ሊያስከትል የሚችል ሌላ ጥፋት ደግሞ የፈጸመ እንደሆነ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

፫/ ባለፈቃዱ ግለሰብ ሲሆን የሞተ እንደሆነ ወይም የንግድ ድርጅት ሲሆን በፍርድ ቤት የመክሰር ውሳኔ የተሰጠበት ወይም የፈረሰ እንደሆነ የወራሾች መብት እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ምዕራፍ መሠረት የተሰጠ ፈቃድ ይሰረዛል፡፡

፬/ ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ከማገዱ ወይም ከመሰረዙ በፊት ፈቃዱ የሚታገድበትን ወይም የሚሠረዝበትን ምክንያት በመግለጽ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ለባለፈቃዱ መስጠት አለበት፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ማስጠንቀቂያ የደረሰው ባለፈቃድ የተሰጠው ፈቃድ ሊሰረዝበት ወይንም ሊታገድበት እንደማይገባ የሚያነሳውን ተቃውሞ ወይም መከላከያ ግልጽ አድርጎ በ፲፭(በአሥራ አምስት) ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፡፡

፮/ ባለሥልጣኑ የባለፈቃዱ መከላከያ ወይም ተቃውሞ በቂና አሳማኝ ሆኖ ያላገኘው እንደሆነ ወይም ባለፈቃዱ በ፲፭ (በአሥራ አምስት) ቀናት ውስጥ ምንም መከላከያ ወይም ተቃውሞ ያላቀረበ እንደሆነ ፈቃዱን በሙሉ ወይም በከፊል አግዶ ወይም ሰርዞ በ፲፭ (በአሥራ አምስት) ቀናት ውስጥ ስለእገዳው ወይም ስለስረዛው ለባለፈቃዱ በጽሁፍ ያሳውቃል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም የተወሰደውን እርምጃ ለህዝብ ማስታወቅ ይችላል፡፡

c) failure to submit a complete report as required pursuant to this Regulation or submission of false report or failure to maintain appropriate documentations;

d) intentionally obstruct or create obstacles in the regulatory activity of the Authority;

e) transferring license issued by the Authority to a third party without the consent of the Authority.

2/ A license of any person may be revoked, if the person fails to rectify the problem entailed suspension within the period given to rectify it, or commits another problem for the second time within two years which may entail suspension.

3/ A license issued under this Chapter shall be revoked, without prejudice to the right of heirs, if the licensee individual dies or where the licensee business organization is liquidated or declared bankrupt.

4/ The Authority shall, before taking the suspension or revocation measure, issue written notice to the licensee by clearly stating the grounds of suspension or revocation of the license.

5/ The licensee received a notice pursuant to sub-article (4) of this Article shall, within 15 (fifteen) days, submit written objection or defence statement to the Authority by clearly stating the reason why the license shall not be suspended or revoked.

6/ If the Authority finds the defense or objection submitted by the licensee not sufficient enough or if the licensee failed to submit any defense or objection within 15(fifteen) days, it shall partly or fully suspend or revoke the license and communicate the licensee in writing within 15(fifteen) days after such action is taken; as appropriate may notify its action public.

፵. ስለአገልግሎት ክፍያ

የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ፣ ኦዲት ተቋራጮነት ወይም የማማከር አገልግሎቶች ፈቃድ ማመልከቻ መመርመሪያ፣ ለጽሁፍና ለተግባር ፈተና ማካሄጃ፣ ፈቃድ ለመስጠት፣ ለማደስ እና ለመተካት በባለስልጣኑ የሚፈጸመው የአገልግሎት ክፍያ መጠን ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው በሰንጠረዥ ፩ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፵፩. የባለፈቃዱ መብቶችና ግዴታዎች

፩/ በዚህ ደንብ ክፍል አምስት መሠረት የተሰጠን ፈቃድ የያዘ ማንኛውም ባለፈቃድ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል:-

ሀ) በመላው ሀገሪቱ ውስጥ በፈቃዱ የተመለከቱ ተግባራትን የማከናወን፣

ለ) በፈቃዱ የተጠቀሰውን አገልግሎት ለመስጠት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የመጠየቅና የማግኘት፣ እና

ሐ) በፈቃዱ መሠረት በቂ አገልግሎት ለሰጠበት ተገቢውን ክፍያ የማግኘት፡፡

፪/ በዚህ ደንብ ክፍል አምስት መሠረት የተሰጠን ፈቃድ የያዘ ማንኛውም ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል:-

ሀ) በአዋጁ፣ በዚህ ደንብ፣ ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ እና በፈቃድ ሁኔታዎች መሠረት የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ተግባራትን የማከናወን፣

ለ) ከደንበኛው ጋር በተደረሰው ስምምነት መሠረት አገልግሎት የመስጠት፣

ሐ) ከመጨረሻ ውይይት በኋላ የክንውን ኦዲት ሪፖርቱን ኦዲት ለተደረገው አካል በአንድ ወር ውስጥ የማቅረብ፣

መ) ለደንበኞች አቤቱታ ወዲያውኑ ምላሽ የመስጠት፣

40. Service Fee

The rate of service fees to be paid for the Authority for examination of application, administration of theory and practical examination; issuance, renewal or replacement of energy efficiency and conservation audit, contracting or consultancy services license shall be prescribed in the table 1 annexed with this regulation.

41. Rights and Obligations of Licensee

1/ Any licensee who has been issued license pursuant to Section Five of this Regulation shall have the following rights:

a) perform activities bestowed by virtue of the license throughout the country;

b) request and obtain data necessary to perform the licensed activity; and

c) receive payment for adequate service rendered pursuant to the license.

2/ Any licensee who has been issued license pursuant to Section Five of this Regulation shall have the following obligations:

a) undertake energy efficiency and conservation activities in accordance with the provisions of the Proclamation, this Regulation, directive to be issued to implement this Regulation and terms and conditions of the license;

b) render service as per the agreement reached with the client;

c) submit energy audit report to the client within a month after exit conference undertaken with the client;

d) promptly address customers complaints;

ሠ) በኢነርጂ ብቃት አጠቃቀም ላይ አስፈላጊ መመሪያዎችን ለደንበኞች የመስጠት፤

ረ) የሠራተኛ፣ የገንዘብ፣ የንግድ እና ሌሎች መዝገቦችን እና ሪከርዶችን ቢያንስ ለ፭ (ለአምስት) ዓመታት የመያዝ፤

ሰ) በባለሥልጣኑ ሲጠየቅ መዛግብትን ለቁጥጥር ሥራ የማቅረብ፤

ሸ) ለሠራተኞቹ አግባብ የሆነ ሥልጠና የመስጠት፤እና

ቀ) የተሰረዘ ፈቃድ ለባለስልጣኑ የመመለስ፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባን ስለማስተዋወቅ እና መቆጣጠር

**፵፪. አጠቃላይ መርሆዎች**

፩/ ባለሥልጣኑ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ የቁጥጥር እርምጃዎችን ለመተግበር በእርምጃዎቹ ጥቅሞች ላይ ትኩረት በማድረግ ለግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ የእርምጃዎችን ባህሪ እና የሚያመጡትን ጥቅም መሠረት በማድረግ የኢነርጂ ቁጠባ የቁጥጥር እርምጃዎችን ደረጃ በደረጃ መፈጸም አለበት፡፡

**፵፫. የባለፈቃዶችን የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ሥራዎች ስለመቆጣጠር**

፩/ ባለሥልጣኑ የኢነርጂ ኦዲት፣ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ተቋራጭነት ወይም የማማከር አገልግሎት ተግባራትን ለማከናወን ፈቃድ በተሰጣቸው ሰዎች ላይ የቁጥጥር ተግባር የሚያካሂድ ተቆጣጣሪ ሠራተኛ ይመድባል፡፡

፪/ በባለሥልጣኑ የተመደበ ተቆጣጣሪ ሠራተኛ በማንኛውም የሥራ ሰዓት ከባለሥልጣኑ የተሰጠውን መታወቂያ በማሳየት የባለፈቃዱን የኢነርጂ ኦዲት፣ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ተቋራጭነት ወይም የማማከር አገልግሎትን መቆጣጠር ይችላል፡፡

e) provide appropriate guidelines and instructions to customers on energy efficiency and conservation;

f) maintain files and records of employees, transaction, finance, and others at least for 5(five) years;

g) make available records to the Authority for inspection;

h) provide proper training to its employees; and

i) surrender the revoked license to the Authority.

## CHAPTER TWO

## PROMOTING AND REGULATING ENERGY EFFICIENCY AND CONSERVATION

**42. General Principles**

1/ The Authority shall, for implementing energy efficiency and conservation regulatory measures, give priority for awareness creation focusing on the benefits of such measures.

2/ The Authority shall implement energy efficiency and conservation regulatory measures phase by phase based on the characteristics and the benefit it brings.

**43. Inspection of Licensees' Energy Efficiency and Conservation Activities**

1/ The Authority shall assign inspection officer to supervise the activities of energy audit, energy efficiency and conservation contracting or consultancy services of licensees.

2/ The inspection officer assigned by the Authority, up on showing his identity card issued by the Authority, at any working hours, may inspect or supervise the activity of energy audit, energy efficiency and conservation contracting or consultancy service of licensees.

፫/ ተቆጣጣሪ ሠራተኛው ቁጥጥር በሚያከሂድበት ወቅት ማናቸውንም የባለፈቃዱን የኢነርጂ ኦዲት፣ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ተቋራጭነት ወይም የማማከር አገልግሎት ሰነዶች፣ ሪከርዶች፣ መገልገያዎች እና ሌሎች ማናቸውም ለቁጥጥሩ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች እንዲቀርቡ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፬/ ተቆጣጣሪ ሠራተኛው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) መሠረት ስላከሄደው የቁጥጥር ተግባር ለባለሥልጣኑ የጽሁፍ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

፭/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) መሠረት በተካሄደው የቁጥጥር ተግባር ባለፈቃዱ የኢነርጂ ኦዲት፣ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ተቋራጭነት ወይም የማማከር አገልግሎት ተግባራትን ሲያከናውን ይህን ደንብ እና ደንቡን ለማስፈጸም በወጣው መመሪያ የተመለከቱትን ማናቸውንም ግዴታዎች ጥሶ የተገኘ እንደሆነ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ ባለሥልጣኑ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት አለበት፡፡

፮/ ባለፈቃዱ በጽሁፍ ማስጠንቀቂያው ውስጥ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማስተካከያ እርምጃ ያልወሰደ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ፈቃዱን እንደሁኔታው ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ይችላል፡፡

**፵፬. <u>ሪፖርት ስለማድረግ</u>**

፩/ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ተግባራትን ለማከናወን ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ስለሥራውና ስለክንውኑ በየዓመቱ ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

፪/ ባለስልጣኑ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ሪፖርት የሚቀርብበትን ቅጽ በመመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

3/ The inspection officer while conducting supervision, may require the licensees to submit documents, records, tools, any other informations related to works of energy audit, energy efficiency and conservation contracting or consultancy services which are necessary for the supervision task.

4/ The inspection officer shall submit a written report to the Authority on the supervision activity he has conducted pursuant to sub-article (2) and (3) of this Article.

5/ The Authority shall issue a written notice to the licensee in order to take appropriate corrective measure; if the supervision made pursuant to sub-article (2) and (3) of this Article shows that the activity of energy audit, energy efficiency and conservation contracting or consultancy service of the licensee violates any of its obligations provided under this Regulation and directive issued to implement this Regulation.

6/ If the licensee fails to take corrective measures within the period determined in the notice, the Authority may, as appropriate, suspend or revoke the license.

**44. <u>Reporting</u>**

1/ Any person who has been issued license to undertake energy efficiency and conservation activities shall report annually to the Authority about its activity and accomplishment.

2/ The Authority may through directive prescribe appropriate form to be followed for submitting energy efficiency and conservation report.

## ምዕራፍ ሦስት

## ስለኤሌክትሪክ ዕቃዎች እና መገልገያዎች

### ፵፭. ስለኢነርጂ ብቃት አፈጻጸም ደረጃ

ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ ፬(፮) መሠረት የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን እና መገልገያዎችን ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የኢነርጂ ብቃት የአፈጻጸም ደረጃ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

### ፵፮. ስለኤሌክትሪክ ዕቃዎች እና መገልገያዎች

፩/ ማንኛውም የኤሌክትሪክ ዕቃ እና መገልገያ አምራች፣ አስመጪ፣ አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ አስገዳጅ የብሔራዊ የኢነርጂ ብቃት ደረጃዎችን የሳሟላ እና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያልተሰጠውን የኤሌክትሪክ ዕቃ እና መገልገያ ማምረት፣ ማስመጣት፣ በጅምላም ሆነ በችርቻሮ መሸጥ፣ ማከራየት ወይም በማናቸውም መልኩ በኢትዮጵያ ገበያ ውስጥ ገብቶ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ አይችልም፡፡

፪/ ማናቸውም የኤሌክትሪክ ዕቃዎች እና መገልገያዎች አምራች ወይም አስመጪ ብሔራዊ የኢነርጂ ብቃት ደረጃ የወጣላቸውን የኤሌክትሪክ ዕቃዎች እና መገልገያዎች ከማምረቱ ወይም ከማስመጣቱ በፊት በዚህ ደንብ መሠረት በሚወጣ መመሪያ ከባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡

፫/ የኤሌክትሪክ ዕቃዎችና መገልገያዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥርዓት ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

፬/ ባለሥልጣኑ የሚጠበቀውን የኢነርጂ ብቃት ተለጣፊ ምልክት እና ዝቅተኛ የኢነርጂ ብቃት አፈጻጸም ደረጃዎችን ባላከበሩ አምራቾች፣ አስመጪዎች፣ ጅምላ ሻጮች ወይም ቸርቻሪዎች ላይ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስድ አግባብነት ላለው ፈቃድ ሰጪ አካል ሊያሳውቅ ይችላል፡፡

## CHAPTER THREE

## ELECTRICAL EQUIPMENTS AND APPLIANCES

### 45. Energy Efficiency Performance Standard

In accordance with Article 4(6) of the Proclamation, the Authority shall cause to set the minimum or maximum energy efficiency performance standard for equipments and appliances.

### 46. Electric Equipment's and Appliances

1/ No. manufacturer, importer, wholesale or retailer of electric equipment and appliance shall produce, import, wholesale or retail, lease or put to use in any way in the Ethiopian market for circulation an electric equipment and appliance which do not comply with mandatory national standards of energy efficiency or do not have certificate of efficiency.

2/ Any manufacturer or importer of electric equipments and appliances for which mandatory national standard of energy efficiency have been developed shall obtain certificate of competency pursuant to a directive to be issued to implement this Regulation ,from the Authority before manufacturing or importing of such electrical equipments and appliances.

3/ The procedure for issuance of certificate of competency for electrical equipments and appliances shall be determined in a directive to be issued implement this Regulation.

4/ The Authority may notify the relevant licensing authority to take necessary measures on those manufacturers, importers wholesalers or retailers who fail to comply with the required energy efficiency labels or minimum energy efficiency performance standards.

**፵፯. ስለኤሌክትሪክ ዕቃዎች እና መገልገያዎች ተለጣፊ ምልክት**

፩/ ማንኛውም ሰው አስገዳጅ የተለጣፊ ምልክት የሚጠይቅን ማናቸውንም የኤሌክትሪክ እቃ እና መገልገያ ተለጣፊ ምልክት ሳያደርግ ማምረት፣ ማስመጣት፣ በጅምላ ወይም በችርቻሮ መሸጥ አይችልም፡፡

፪/ ተለጣፊ ምልክቱ የኤሌክትሪክ ዕቃውን እና የመገልገያውን የኢነርጂ ብቃትና ሌሎች ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ የሚወሰኑ አስፈላጊ መረጃዎችን መያዝ አለበት፡፡

፫/ ተለጣፊ ምልክቱ በእያንዳንዱ የኤሌክትሪክ እቃ መገልገያ እና ማሸጊያ ላይ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ መጻፍ እና ግልጽ ቦታ ላይ መለጠፍ አለበት፡፡

፬/ ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ መሠረት ተለጣፊ ምልክት የተደረገበትን የኤሌክትሪክ እቃ ወይም መገልገያ ለመጀመሪያ ቸርቻሪ ከመሸጡ ወይም ለመጀመሪያ ተከራይ ከማከራየቱ በፊት በምርቱ ወይም በማሸጊያው ላይ የተለጠፈውን ማናቸውንም የኢነርጂ ብቃት ተለጣፊ ምልክት ማስወገድ፣ ማበላሸት፣ መደበቅ ወይም መለወጥ የለበትም፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ማንኛውም ሰው በተለጣፊ ምልክቱ ላይ ስላለው መረጃ ትክክለኛነት ኃላፊነት አለበት፡፡

፮/ ባለሥልጣኑ የኢነርጂ ብቃት እና ቆጣቢ ዕቃዎች እና መገልገያዎች ወይም የማሸጊያቸውን ተለጣፊ ምልክት ቅርጽ፣ ይዘት፣ ዓይነት፣ ምልክት እና ዝርዝር ሥርዓቶችን አስመልክቶ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**47. Labeling of Electrical Equipments and Appliances**

1/ No person shall manufacture, import, wholesale or retail any electrical equipment and appliance that has not been labeled for which mandatory labeling standard is required.

2/ The label shall contain energy efficiency of electric equipment and appliance, and other appropriate informations to be prescribed by directive to be issued to implement this Regulation.

3/ The label shall be affixed in Amharic and English language and placed in a conspicuous position on every electrical equipment and appliance and their packages.

4/ No person shall remove, deface, obscure or alter any energy efficiency label affixed according to this Regulation on energy efficiency of electric equipment and appliance or its package before such labeled equipment and appliance is sold to the first retail purchaser or leased to the first lessee.

5/ Any person which indicated under sub-article (1) of this Article shall be responsible for the accuracy of the information on the energy efficiency labels.

6/ The Authority may issue directive on the form, content, type, symbol and procedure of labeling of energy efficiency of electrical equipments and appliances and their package.

**፵፰. ስለኤሌክትሪክ ዕቃዎች እና መገልገያዎች የኢነርጂ ብቃት ፍተሻ**

፩/ ባለሥልጣኑ እንደአስፈላጊነቱ ማንኛውም አምራች ወይም አስመጪ የኤሌክትሪክ ዕቃውን እና መገልገያውን የኢነርጂ ብቃት እንዲያስፈትሽ ባለሥልጣኑ በሚገልጸው ቦታ እና በባለሥልጣኑ የተመረጡ ናሙናዎችን እንዲያቀርብ ሊጠየቅ ይችላል፤ አምራቹ ወይም አስመጪውም በጥያቄው መሠረት የኤሌክትሪክ ዕቃውን እና መገልገያውን የማቅረብ እና የማስፈተሽ ግዴታ አለበት፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ ናሙናዎችን በመምረጥ ከገበያ ላይ በመግዛት መፈተሽ ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የፍተሻ ሥራው ናሙናውን መፈታታትንና መክፈትን ግድ የማይል ከሆነና ንብረቱ ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት የማያስከትል ሲሆን ፍተሻውን ያለፉት ናሙናዎች ለአስመጪው ወይንም ለአምራቹ ይመለሳሉ፡፡

፬/ ለፍተሻ ሥራው የቀረቡ ናሙናዎች ተመልሰው አገልግሎት ሊሰጡ በማይችሉበት ሁኔታ መፈታታትን ግድ የሚሉ ከሆነ ፍተሻውን ቢያልፉም ናሙናዎቹ እስካልተጠየቁ ድረስ ለአስመጪው ወይም ለአምራቹ ላይመለሱ ይችላሉ፡፡

፭/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የቀረበለትን ማናቸውንም የኤሌክትሪክ ዕቃ እና መገልገያ ናሙና በትኖ ሊመረምር እንዲሁም የኢነርጂ ብቃቱን በአግባቡ ለመወሰን አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ሌሎች የፍተሻ ዘዴዎችንም ሊጠቀም ይችላል፤ ሆኖም የፍተሻውን ዘዴ እንደየአግባቡ ለአምራቹ ወይም ለአስመጪው በቅድሚያ ማሳወቅ አለበት፡፡

**48. Energy Efficiency Testing of Electrical Equipments and Appliances**

1/ The Authority may, as appropriate, require any manufacturer or importer of electrical equipment and appliance to make available samples identified by the Authority, at such place the Authority may specify for testing of their energy efficiency and the manufacturer or importer shall have obligation to avail and comply with this request.

2/ Without prejudice to sub-article (1) of this Article, the Authority may directly purchase samples of its choice from the Market and test their energy efficiency.

3/ Where the test conducted pursuant to sub-article (1) of this Article does not involve destructive testing, those samples which have passed the test shall be returned to the manufacturer or importer.

4/ Where the testing procedure involves destructive tests where after test procedure conducted, the samples may not fit to use, such samples may not be returned to the manufacturer or importer unless requested otherwise.

5/ The Authority may dismantle and examine any electrical equipment and appliance made available pursuant to sub-article (1) of this Article and may conduct such tests as the Authority considers reasonably necessary to determine its energy efficiency; provided, however that the Authority may in advance, as appropriate, notify the test procedures to the manufacturer and importer.

፮/ ባለሥልጣኑ የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን እና መገልገያዎችን የኢነርጂ ብቃት ለማስፈተሽ አግባብነት ካለው አካል ጋር ስምምነት ሊገባ ይችላል፡፡

6/ The Authority may enter into an agreement with an appropriate body for testing the energy efficiency of the electrical equipments and appliances.

## ምዕራፍ አራት
## በኢንዱስትሪዎች የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ

## CHAPTER FOUR
## ENERGY EFFICIENCY AND CONSERVATION IN INDUSTRIES

### ፵፱. ጠቅላላ መርሆዎች

፩/ በኢንዱስትሪዎች ውስጥ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ተግባራት የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡-

ሀ) የኢነርጂ ብክነት መከላከልን፣

ለ) የቀዳሚ ኢነርጂ ምንጭ መቀጣጠል መሻሻልን፣

ሐ) የኢነርጂ ተረፈ ምርትን መልሶ መጠቀምን፣

መ) አንድን የኢነርጂ ዓይነት በሌላ መተካትን፣

ሠ) ፓወር ፋክተርን በማሻሻል የኤሌክትሪክ አጠቃቀምን የበለጠ ብቁ ማድረግን፣

ረ) በሲስተሙ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ፍላጎት በሚኖርበት ጊዜ ከፍተኛ የኃይል ፍላጎትን መቀነስን፣

ሰ) ደረጃቸውን የጠበቁ ዕቃዎች መጠቀምን፣ እና

ሸ) የኢነርጂ ብቃት ያለው መሣሪያ ወይም ዕቃ እንዲሁም ለኢነርጂ ቁጠባ አስተዋጽዖ የሚያደርጉ የኦፕሬሽን መቆጣጠሪያ ሲስተሞችን መጠቀምን፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ ተጨማሪ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ዘዴዎችን ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

### ፶. ስለተመረጡ ኢንዱስትሪዎች

፩/ ባለሥልጣኑ ይህን ደንብ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ መሠረት ኢንዱስትሪዎችን በዓይነት፣ በኢነርጂ ፍጆታ ወይም በኢነርጂ አጠቃቀም ዘዴ መምረጥ ይችላል፡፡

### 49. General Principles

1/ Energy efficiency and conservation activities in industries may include the following:

a) prevention of energy loss;

b) improvement in combustion or conversion of primary energy sources;

c) recycling of energy wastes;

d) substitution of one type of energy by another;

e) more efficient use of electricity through improvements in power factors;

f) reduction of maximum power demand during the period of the electricity system's peak demand;

g) using of appropriate standard equipment's; and

h) use of energy-efficient machinery or equipment as well as the use of operation control systems that contribute to energy conservation and through other approaches.

2/ Without prejudice to the provisions of sub-article (1) of this Article, additional means of energy efficiency and conservation mechanisms may be determined in a directive to be issued hereunder.

### 50. Designated Industries

1/ The Authority may designate industries based on their type, quantities of energy consumption, or methods of energy utilization through directives to be issued to implement this regulation.

፪/ የተመረጠው የኢንዱስትሪ ባለቤት ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ፣ ደረጃ፣ ቅድመ ሁኔታዎችና ሥርዓቶች መሠረት፦

ሀ) የኢንዱስትሪውን የኢነርጂን ፍጆታ መቆጠብ፣

ለ) በተወሰነ ጊዜ ገደብ የኢንዱስትሪውን የኢነርጂ አጠቃቀም ኦዲት ማስደረግ እና መተንተን፣

ሐ) የኢንዱስትሪውን የኢነርጂ አጠቃቀም መረጃዎችን ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ማድረግ፣ እና

መ) የፈቃደኝነት ስምምነት መግባት፣ አለበት፡፡

፫/ ባለስልጣኑ የተመረጡ ኢንዱስትሪዎች ተግባራዊ ማድረግ ያለባቸውን የኢነርጂ አጠቃቀምን ለማሻሻል የሚያስችሉ እርምጃዎችን በተመለከተ ትዕዛዝ መስጠት ይችላል፡፡

## ፶፩. ስለተመረጠ ኢንዱስትሪ ባለቤት ግዴታዎች

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፲፱ (፬) እና (፭) እንዲሁም አንቀጽ ፳፪(፬) መሠረት ማንኛውም የተመረጠ የኢንዱስትሪ ባለቤት የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፦

ሀ) በኢንዱስትሪው ውስጥ ለኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ እርምጃዎች ሙሉ ኃላፊነት እና ብቃት ያለው ቢያንስ አንድ ባለሙያ የመመደብ፣

ለ) የኢነርጂ ፍጆታ፣ የምርት እና የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ እርምጃዎችን በተመለከተ ለባለሥልጣኑ ሪፖርት የማቅረብ፣

ሐ) ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ ከሚደነገጉት ቅድመ ሁኔታዎች እና ሥርዓቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በኢነርጂ ፍጆታ እና በኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ የኢንስታሌሽን፣ የማሽን ለውጥ ወይም የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን እና መገልገያዎችን መዝግቦ የመያዝ፣

2/ The owner of the designated industry, in accordance with the directive, standard, criteria and procedures to be issued, shall:

a) conserve energy consumption of the industry;

b) periodically audit and analyze energy utilization of the industry;

c) report energy profile of the industry to the Authority; and

d) enter voluntary agreement;

3/ The Authority may give instructions regarding measures to be taken by the designated industry to improve energy performance which the industry shall put into effect.

## 51. Obligations of Owner Designated Industry

1/ The owner of any designated industry, in accordance with Article 19 (4) and (5)and Article 22 (4) of the Proclamation shall have the following obligations:

a) to assign at least one qualified person who is in charge of full responsibility to the designated industry with regard to energy efficiency and conservation measures;

b) to submit report on energy consumption, production, and energy efficiency and conservation measures to the Authority;

c) to keep records of report on energy consumption and installation or modification of machinery or electrical equipments and appliances that affect energy consumption energy efficiency and conservation, in compliance with the criteria and procedures to be prescribed in the directive to be issued to implement this Regulation;

መ) ከኢነርጂ ጋር የተያያዙ መዝገቦችን ቢያንስ ለ፭(ለአምስት) ዓመታት የማቆየት፣

ሠ) ከመመዘኛዎች፣ ሥርዓቶች እና የጊዜ ሰሌዳዎች ጋር በማጣጣም ለኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ለማሳካት ግብ እና ዕቅድ በማውጣት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ እና የተመረጠ ኢንዱስትሪ ሥራን ኦዲት እና ትንተና የማድረግ፣ እና

ረ) በተመረጠ በ፩፻፹(በአንድ መቶ ሰማንያ) ቀናት ውስጥ ስለኢንዱስትሪው ለባለሥልጣኑ ሪፖርት የማድረግ፡፡

፪/ የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ለ)፣ (መ) እና (ሠ) በአግባቡ ለማስፈጸም የሚያግዙ ቅጾች፣ መመዘኛዎች፣ ሥርዓቶች እና የጊዜ ሰሌዳዎች ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ ይወሰናሉ፡፡

## ፶፪. ስለፈቃደኝነት ስምምነት

፩/ ቀጣይነት ላለው የኢነርጂ ብቃት መሻሻል በአዋጁ አንቀጽ ፳፪ መሠረት ባለሥልጣኑ ከእያንዳንዱ አግባብ ካለው ከተመረጠ ከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚ ኢንደስትሪዎች፣ እንደ የአግባቡም ከኢነርጂ መሣሪያዎች እና መገልገያዎች አምራቾች ወይም አስመጪዎች ጋር የፈቃደኝነት ስምምነት መደራደር፣ መፈራረምና መፈጸም ይችላል፡፡

፪/ የፈቃደኝነት ስምምነቱ ተመሳሳይነት ካላቸውና ከተመረጡ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ በተግባር የዋሉ የኢነርጂ ብቃት ማሻሻያ እርምጃዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት እና ብቃትን ደረጃ በደረጃ ሊያሻሽሉ የሚችሉ የተረጋገጡና ከሁኔታዎች ጋር የተጣጣሙ እርምጃዎችንም ሊያካትት ይገባል፡፡

፫/ የፈቃደኝነት ስምምነቱ የኢነርጂ ብቃት መሻሻልን በተመለከተ ከእያንዳንዱ የማሻሻያ እርምጃ በዓመት ውስጥ የሚጠበቀውን ውጤት በመቶኛ የሚያመላክት መሆን አለበት፡፡

d) keep the records related to energy for a minimum of 5(five) years;

e) to audit and analyze operations of the designated industry to achieve such targets and plans, for energy efficiency and conservation, in compliance with the criteria, procedures and schedules; and

f) to report to the Authority about the industry with 180 (one hundred eghity) days after it has been designated.

2/ The Authority may issue a directive that specifies the forms, criteria, procedures and schedules for the proper implementation of sub-article (1) (b), (d) and (e) of this Article.

## 52. Voluntary Agreement

1/ For a sustainable improvement of energy efficiency; the Authority may negotiate, and sign a voluntary agreement, and execute same, in accordance with Article 22 of the Proclamation, with the designated high energy consuming industries or with energy consuming electrical equipments and appliances manufacturers or importers, as may be appropriate, concerning relevant energy consuming facilities or appliances or equipments.

2/ The voluntary agreement shall take in to account the energy efficiency improvement measures being implemented at energy consuming facilities belonging to the same designated industries and include definite, relevant measures to improve energy efficiency.

3/ The voluntary agreement shall indicate the expected result of each of this improvement measure, expressed as a percentage of energy efficiency improvement per annum.

፬/ ማንኛውም የተመረጠ ኢንዱስትሪ ባለቤት የፈቃደኝነት ስምምነቱ በአግባቡ ስለመፈጸሙ፣ የኢነርጂ ብቃት ስኬቱን በመቶኛ እንዲሁም ያጋጠመውን ማናቸውንም ሌላ መሰናክል በመግለጽ በስምምነቱ ላይ በሚገለጸው የአቀራረብ አግባብ ወቅታዊ ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

፭/ ባለሥልጣኑ የሪፖርቱን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ተጨማሪ መረጃዎችን በመጠየቅ ወይም በአካል በመገኘት በሪፖርቱ የተጠቀሱትን ጉዳዮች ትክክለኛነት ሊያጣራ ይችላል፡፡

፮/ በአዋጁ አንቀጽ ፳፪ (፬) መሠረት የፈቃደኝነት ስምምነቱ በተገባው ውል መሠረት ያለበቂ ምክንያት ያልተፈጸመ እንደሆነ ባለስልጣኑ አስተዳደራዊ መቀጫ ሊወስን ይችላል፡፡

## ፶፫. ስለኢነርጂ አስተዳደር ክፍል

፩/ የተመረጠው ኢንዱስትሪ ባለቤት በተመረጠው ኢንዱስትሪ ውስጥ ሙሉ ኃላፊነትን ወስዶ ከኢነርጂ ፕሮግራም አንጻር የሚሰራ የኢነርጂ አስተዳደር ክፍል ማቋቋም እና ባለሙያዎችን መመደብ አለበት፡፡

፪/ የኢነርጂ አስተዳደር ክፍል ሠራተኞች በኤሌክትሪካል ወይም ኤሌክትሮ-መካኒካል ወይም በሌላ አግባብ በሆነ የምህንድስና መስክ የተማሩ እና የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ኃላፊነትን ለመወጣት ብቁ መሆን አለባቸው፡፡

፫/ የኢነርጂ አስተዳደር ክፍል የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

ሀ) ኢነርጂ የሚጠቀም ማሽንን እና ዕቃን በየወቅቱ የመጠገን እና ብቃቱን የመፈተሽ፣

ለ) የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ መርህን ተከትሎ የኢነርጂ ፍጆታን የማሻሻል፣

4/ The owner of any designated industry shall submit periodic report, the frequency of which as defined in the agreement, to the Authority specifying the proper implementation of the voluntary agreement, achievement of energy efficiency in percentage and any other limitations encountered.

5/ The Authority may by requesting additional informations or physical inspection can confirm the accuracy of such a report.

6/ In accordance with Article 22(4) of the Proclamation, where such voluntary agreement is, for any reason not sufficient, failed to be implemented the Authority could impose administrative fines.

## 53. Energy Management Unit

1/ The owner of a designated industry, shall establish energy management unit and assign professionals staffs at the designate industry to take full responsibility with regard to the energy program.

2/ The energy management unit staff shall be qualified in electrical or mechanical or in any other relevant field of engineering and competent to undertake the responsibilities of energy efficiency and conservation programs.

3/ The energy management unit shall have the following responsibilities:

a) periodically maintain and inspect the efficiency of machinery and equipment that consumes energy;

b) improve energy consumption in line with the principle of energy efficiency and conservation;

ሐ) በባለሥልጣኑ ለተመደበ ተቆጣጣሪ ወይም ባለፈቃድ የመዛግብቱን ትክክለኛነት ለመፈተሽ እና ለማረጋገጥ እንዲችል መረጃ መያዙን የማረጋገጥ፣

መ) የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ግቦች እና ዕቅዶች ዝግጅትን የማገዝ፣ እና

ሠ) የምርመራ እና የግምገማ ውጤቶችን ትክክለኛነት የማረጋገጥ፡፡

**፶፬. ስለመረጃ ስርጭት**

ባለሥልጣኑ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ መረጃን እና አግባብነት ያለውን ማናቸውንም ሌላ መረጃ ለማሰራጨት የትምህርት ተቋማትን፣ የፌደራል እና የክልል መንግሥታት ተቋማትን፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ አገልግሎት አቅራቢዎችን፣ የንግድ ድርጅቶችን፣ የሙያ እና የኅብረት ሥራ ማህበራትን እና የመሳሰሉትን ሊጠቀም ይችላል፡፡

## ምዕራፍ አምስት
## ስለሕንጻዎች ኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ

**፶፭. ስለሕንጻዎች የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ የቁጥጥር ተግባራት**

፩/ የሕንጻ ኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ቁጥጥር በኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ኮዶች፣ ደረጃዎች ወይም ተለጣፊ ምልክቶች መካከል በአንዱ ወይም በሁሉም ሊካሄድ ይችላል፡፡

፪/ በግንባታ ወይም በጥገና ወቅት የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ እርምጃዎች ታሣቢ እንዲደረጉ በሕንጻ ኮዶች ውስጥ መካተት አለበት፡፡

**፶፮. ስለሕንጻ ኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ዘዴዎች**

፩/ የሕንጻ ኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ከሚከተሉት ዘዴዎች ውስጥ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ሊያካትት ይችላል:-

c) oversee record keeping of information so that the supervisor assigned by the Authority or relevant licensee may inspect and verify the accuracy of such records;

d) assist in setting the goals and plans for energy efficiency and conservation; and

e) verify the result of the inspection or evaluation.

**54. Dissemination of Information**

The Authority may utilize educational institutions, federal, regional states and local government entities, non-governmental organizations, utilities, trade organizations, professional associations and societies to disseminate energy efficiency information and any other relevant information.

## CHAPTER FIVE
## ENERGY EFFICIENCY AND CONSERVATION IN BUILDINGS

**55. Energy Efficiency and Conservation Regulatory activities/actions for Buildings**

1/ Energy efficiency and conservation in building may be regulated through energy efficiency and conservation codes, standards or labels, or through a combination of any or all.

2/ Building codes shall take into account the energy efficiency and conservation measures to be achieved either during construction or maintenance period.

**56. Methods for Energy Efficiency and Conservation in Buildings**

1/Energy efficiency and conservation in building may include any one or more of the following methods:

ሀ) ወደ ሕንጻው የሚገባውን የፀሐይ ብርሃን ሙቀት መቀነስ፣

ለ) ክፍሉን በአስፈላጊው የሙቀት ደረጃ የሚጠብቅ ብቁ የአየር ሙቀት መቆጣጠሪያ መሣሪያዎችን መጠቀም፣

ሐ) ኢነርጂ ቆጣቢ የሆኑ የሕንጻ ግንባታ ዕቃዎችን መጠቀም፣

መ) በቂ የተፈጥሮ ብርሃንን በሕንጻው ውስጥ መጠቀም፣ ወይም

ሠ) በሕንጻው ውስጥ ለኃይል ቁጠባ አስተዋጽዖ የሚያደርጉ ዕቃዎችን እና መሣሪያዎችን መትከልና መጠቀም፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ቢኖርም ስለሕንጻው የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ተጨማሪ ዘዴዎች ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ ሊወሰን ይችላል፡፡

## ፶፯. ስለተመረጡ ሕንጻዎች

፩/ ባለሥልጣኑ ይህን ደንብ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ ሕንጻዎችን በዓይነት፣ በስፋት፣ በኢነርጂ ፍጆታ መጠን ወይም በኢነርጂ አጠቃቀም ዘዴ ሊመርጥ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በባለሥልጣኑ የሚወጣ መመሪያ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

ሀ) የሕንጻውን አጠቃላይ ሙቀት የማስተላለፍ አቅም እና የኢነርጂ ፍጆታ፣

ለ) የሕንጻውን ሙቀት የማስተላለፍ አቅም መገመገሚያ መመዘኛዎች፣ ሥርዓቶች እና ሁኔታዎች፣ የግንባታ መሣሪያዎች አጠቃላይ ሙቀት የማስተላለፍ አቅም እንዲሁም የኢነርጂ አጠቃቀም፣ እና

ሐ) የሕንጻውን የአየር ሁኔታ መቆጣጠሪያ ዘዴውን፣ የሚጠቀመውን ውሃና አካባቢን የማሞቂያ ቴክኖሎጂ፡፡

a) reduction of heat from the sunlight that enters in to the building;

b) Use of efficient air conditioning, maintaining room temperature at appropriate level;

c) use of energy efficient construction materials.

d) efficient use of natural light in the building; or

e) installation and use of machinery, equipment, and materials that contribute energy conservation in the building;

2/ Notwithstanding the provision of sub-article (1) of this Article, additional methods of energy efficiency and conservation in building may be provided through directive to be issued to implement this Regulation.

## 57. Designated Buildings

1/ The Authority may designate buildings based on their type, size, quantity of energy use, or method of energy utilization through directive to be issued to implement this Regulation.

2/ The directive to be issued by the Authority in accordance with sub-article (1) of this Article shall contain the following:

a) the overall thermal transfer value and energy consumption of the building.

b) criteria, procedures and conditions for estimation of the thermal transfer, value of construction materials and the overall thermal transfer value, as well as energy utilization of the building; and

b) Standard for air conditioning, hot water generation and space heating systems of the building.

፫/ የተመረጠው ሕንጻ ባለቤት የሕንጻውን ኢነርጂ ፍጆታ ለመቆጠብ አግባብነት ያለውን እርምጃ መውሰድና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በሚወጣ መመሪያ በተመለከቱ መስፈርቶችና አሰራሮች መሠረት የሕንጻውን ኢነርጂ ፍጆታ ማስተንተን አለበት፡፡

፬/ ማንኛውም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተመረጠ ሕንጻ ፈቃድ ባለው ኢነርጂ ኦዲተር፣ ተቋራጭ ወይም አማካሪ በየሦስት ዓመቱ ኦዲት መደረግ አለበት፡፡

## ምዕራፍ ስድስት

## ስለኢነርጂ ብቃት እና ቆጠባ ፈንድ

**፶፰. ፈንዱ ለሚከተሉት ዓላማዎች ይውላል**

፩/ ቦርዱ ኢንዱስትሪዎች፣ ሕንጻዎች እና ሌሎች የንግድ ድርጅቶች አስቀድሞ በተካሄደ የኢነርጂ ኦዲት ሪፖርትና መነሻ ጥናትን መሠረት በማድረግ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ከኢነርጂ ብቃትና ቆጠባ ጋር የተገናኙ ሥራዎችን ለመተግበር ከፈንዱ በመንግሥት የንግድ ባንክ ወለድ ምጣኔ ወይም በአነስተኛ ወለድ ምጣኔ ወይም ከወለድ ነጻ በሆነ ሙሉ ወይም ከፊል ብድር ወይም ሙሉ ወይም ከፊል የብድር ዋስትና ወይም ወጪ በመጋራት መልክ:-

ሀ) ለአጭር፣ ለመካከለኛ እና ለረጅም ጊዜ የኢነርጂ ብቃት እና ቆጠባ ማስፈጸሚያ ፕሮጀክቶች፣

ለ) የኢነርጂ ብቃት እና ቆጠባ ለምርምር እና ለልማት፣ ለማማከር አገልግሎት፣ ለኢነርጂ ኦዲት፣ ለሰርቶ ማሳያ ፕሮጀክቶችና ለአቅም ግንባታ ሥራዎች፣

ሐ) የኢነርጂ ብቃት እና ቆጠባ ለመረጃ ስርጭት እና ተያያዥ ለሆኑ የሕዝብ ግንኙነት ተግባራት፣ ለመሳሰሉት እንዲጠቀሙበት ሊፈቅድ ይችላል፡፡

3/ The owner of the designated building shall conserve energy, audit and analyze energy consumption of the building in accordance with the criteria and procedures indicated under the directive to be issued pursuant to sub-article (2) of this Article.

4/ Any designated building under sub-article (1) of this Article shall undertake an energy audit once every three years and such an energy audit shall be conducted by licensed energy auditor, contractor or consultant.

## CHAPTER SIX

## ENERGY EFFICIENCY AND CONSERVATION FUND

**58. the Fund will have the following purposes;**

1/ The Board, based on energy audit report, and initial studies and reports may, avail finance from the Fund, on government commercial bank interest or low interest or free from interest, partial or full loan or partial or full credit risk guarantee or on cost sharing basis for activities related to energy efficiency and conservation such as:

a) short, medium, and long term energy efficiency and conservation project implementation;

b) consultancy; energy auditing; research and development; demonstration projects; and capacity building activities with regards to efficiency and conservation; and

c) information dissemination, promotional and related public relation activities with regards to efficiency and conservation.

፪/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ፈንዱን ለመጠቀም የሚያስችል ዝርዝር መስፈርት በመመሪያ ይወስናል፡፡

## ፶፱. ስለቦርዱ ሥልጣንና ተግባራት

፩/ ቦርዱ በአዋጁ አንቀጽ ፭ የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ፈንዱን በተመለከተ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) ለፈንዱ የገንዘብ ማግኛ ፖሊሲዎችን የመቅረጽ፤

ለ) ዓላማዎቹን መሠረት በማድረግ የፈንዱን ድልድል የመወሰን፤

ሐ) የፈንዱን ዓመታዊ ግብ የመወሰን፤

መ) በብድር የተሰጠውን ፈንድ በመሰብሰብ ለተመሣሣይ ዓላማ በተዘዋዋሪ ብድርነት ሥራ ላይ እንዲውል የመወሰን፤ እና

ሠ) ከፈንዱ ብድር እና ድጎማ ለማግኘት የጥያቄ አቀራረብ ሥርዓትና የድልደላ መመዘኛ መመሪያ የማዘጋጀት፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ ከፈንዱ አስተዳደር ጋር የተያያዙ የዕለት ተዕለት ተግባራትን ያከናውናል፡፡

፫/ ቦርዱ ፈንዱ በአዋጁ አንቀጽ ፳፫(፪) ለተገለጸው ዓላማ ስለመዋሉ በየጊዜው ክትትል ማድረግ አለበት፡፡

## ፷. ስለፈንዱ አስተዳደር

፩/ የኢነርጂ ቦርድ ስለ ፈንዱ አስተዳደር መመሪያ ያወጣል፡፡

፪/ የኢነርጂ ቦርድ ከተለያየ ምንጭ የሚሰበሰበውን ፈንድ የሚያስተዳድር የገንዘብ ባለአደራ ተቋም በመምረጥ ማፅደቅ አለበት፡፡

፫/ ለፈንዱ የሚደረግ መዋጮ በቅድሚያ ለኢነርጂ ቦርድ በማስታወቅ በባለአደራ ወኪል ዘንድ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡

2/ The Authority pursuant to sub-article (1) of this Article shall issue requirements by a directive regarding utilization of the Fund.

## 59. Power and Duties of the Board

1/ Without prejudice to Article 5 of the Proclamation the Board shall have the following power and duties to:

a) formulate policies to generate money for the Fund;

b) determine the allocation of the Fund based on objectives;

c) determine the annual target of the Fund;

d) determine the Fund to be used as a revolving loan to be collected thereafter; and

e) issue directive with respect to the criteria and procedures of making loan and subsidy request from the Fund and apportioning requirements.

2/ The Authority shall undertake the day-to-day routine activities in relation to the administration of the Fund.

3/ The Board shall monitor from time to time effective utilization of the Fund for the purpose stipulated under Article 23(2) of the Proclamation.

## 60. Administration of the Fund

1/ The Energy Board shall issue a directive for the administration of the Fund.

2/ The Energy Board shall select and approve the nominated trust agent that administers the Fund to be secured from different sources.

3/ The contributions for the Fund shall be paid to a trust agent, following notification to the Energy Board.

## ፷፩. ስለፈንዱ አሰባሰብ

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፳፫(፫) ላይ ከተገለጹት ምንጮች የሚሰበሰበው ገንዘብ በየዓመቱ ተሰብስቦ ለተመረጠው የገንዘብ ባለአደራ ተቋም ገቢ መደረግ አለበት፡፡

፪/ ቦርዱ ፈንዱ በየጊዜው መሰብሰቡን እና በገንዘብ ባለአደራ ተቋሙ ዘንድ መቀመጡን ማረጋገጥ አለበት፡፡

## ፷፪. ስለፈንዱ አጠቃቀም ሪፖርት

በዚህ ደንብ ለተመለከቱት ዓላማዎች ከፈንዱ ብድር ወይም ድጋፍ ያገኙ ተጠቃሚዎች በባለሥልጣኑ በሚዘጋጁ ቅጾች መሠረት የሩብ፣ የግማሽ እና ዓመታዊ ሪፖርት ለቦርዱ ማቅረብ አለባቸው፡፡

## ፷፫. የገንዘብ ባለአደራ ተቋሙ ኃላፊነት

ባለአደራ ወኪሉ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፳፫(፫) ድንጋጌ መሠረት ባለአደራ ወኪሉ ከተለያዩ የፈንዱ ምንጮች የተገኘውን ገቢ የመቀበል እና የማስቀመጥ፤

፪/ ባለአደራ ወኪሉ በቦርዱ ትዕዛዝ ለኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ተግባራት እንዲውል የተወሰነን ብድር ለተበዳሪው መስጠት እና ከተበዳሪው መልሶ የመሰብሰብ፤

፫/ ባለአደራ ወኪሉ በውሉ መሠረት የፈንዱን ገቢ እና ወጪ የሚያሳይ የሩብ፣ የግማሽ እና ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ ማዘጋጀት እና ለቦርዱ የማቅረብ፤

፬/ ከፈንዱ ጋር በተያያዘ በቦርዱ በውል የሚሰጡትን ሌሎች ተጨማሪ ተግባራት የማከናወን፡፡

## 61. Collection of Fund

1/ The Fund shall be collected annually from the specified source stated under Article 23 (3) of the Proclamation has to be deposit to the selected trust agent.

2/ The Board shall ensure the timely collection of Fund and its deposit to the trust agent.

## 62. Reporting on Fund Utilization

Those beneficiaries obtain loan or subsidy from the Fund for the purposes provided under this Regulation shall submit quarterly, biannual and annual report to the Board based on the forms prescribed by the Authority.

## 63. Responsibility of the Trust Agent

The Trust Agent shall have the following responsibilities:

1/ receive and deposit the income accrued from various sources of Fund as provided under Article 23 (3) of the Proclamation;

2/ loan fund money for the energy efficiency and conservation activities upon the order of the Board and shall collect loan payments;

3/ In accordance with the agreement ,prepare financial statement quarterly, biannual and annual revealing the revenues and expenditure of the Fund and submit it to the Board.

4/ The trust agent shall by agreement carry out other additional activities given by the Board.

## ክፍል ስድስት

## አለመግባባትን ስለ መፍታት

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ

### ፷፬. አጠቃላይ መርሆዎች

፩/ ማናቸውም አለመግባባቶች እና አቤቱታዎች በቅድሚያ በተከራካሪ ወገኖች መካከል በሚደረግ የጋራ ስምምነት ሊፈቱ ይችላሉ፡፡

፪/ ተከራካሪ ወገኖች አለመግባባታቸውን በጋራ ስምምነት መፍታት ካልቻሉ አለመግባባታቸው እንዲፈታላቸው አቤቱታቸውን ለባለስልጣኑ ወይም ለአስማሚው ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት አለመግባባቱ በአስማሚው ካልተፈታ በግልግል ዳኝነት እንዲፈታ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የግልግል ዳኝነቱን ውሣኔ የሰጠው ባለስልጣኑ ከሆነ ውሳኔው በተከራካሪዎች ላይ አስገዳጅና የመጨረሻ ይሆናል፡፡

### ፷፭. ከደንበኞች የሚቀርብ አቤቱታን ስለመስማት

፩/ ደንበኛው ባለፈቃዱ ያዘጋጀውን ሁሉንም አቤቱታ የመስማት ሥርዓቶች አሟጦ ከጨረሰ እና በባለፈቃዱ ውሳኔ ያልረካ ከሆነ ወይም ባለፈቃዱ አቤቱታው በደረሰው በአንድ ወር ውስጥ ውሳኔ ካልተሰጠ አቤቱታውን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይችላል፡፡

፪/ ባለፈቃዱ ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ በ፲፭ (በአሥራ አምስት) ቀናት ውስጥ ደንበኛው አቤቱታውን በጽሁፍ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ያለበት ሲሆን ባለሥልጣኑም አቤቱታውን በተቀበለ በ፲፭ (በአሥራ አምስት) ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ባለሥልጣኑ በቀረበለት አቤቱታ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ አስገዳጅና የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## PART SIX

## SETTLEMENT OF DISPUTE

## CHAPTER ONE

## GENERAL

### 64. General Principles

1/ Any disputes and complaints may be settled by the parties themselves at first amicably.

2/ When parties fail to settle their dispute amicably, they may resort either to submit a complaint to the Authority or to a mediator.

3/ When the dispute cannot be resolved through mediation as per sub-article (2) of this Article it may be settled by arbitration.

4/ If the arbitral award under sub-article (3) of this Article is given by the Authority, it shall be final and binding on all parties involved in the arbitration proceeding.

### 65. Handling Complaint of Customers hearing of customers complaint

1/ The customer may submit his complaint to the Authority, where he has exhausted all complaint hearing procedures arranged by the licensee and is not satisfied by the decision of the licensee or the licensee failed to render decision within one month of receiving of such compliant.

2/ The customer shall submit his complaint to the Authority in written form within 15(fifteen) days from the date of final decision of the licensee and the Authority shall render the decision within 15 (fifteen) days of receiving such a complaint.

3/ the decision given by the Authority on complaint submitted to it pursuant to sub-article (2) of this Article shall be binding and final.

## ምዕራፍ ሁለት

## አለመግባባትን በማስማማት ስለመፍታት

### ፷፮. አስማሚ ስለመሰየም

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፷፬ (፩) መሠረት ተከራካሪ ወገኖች አለመግባባታቸውን በስምምነት መፍታት ካልቻሉ አንዱ ወይም ሁሉም ወገኖች ባለሥልጣኑ አስማሚ እንዲሰይም ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አስማሚ እንዲሰየም የሚቀርብ ጥያቄ:-

ሀ) የተከራካሪ ወገኖችን ስም እና አድራሻን፣

ለ) የአለመግባባቱን መንሻ እና ከማስማማት ሂደቱ የሚፈለግ መፍትሄን፣ እና

ሐ) በአስማሚነት እንዲሰየም የታጨውን ሰው ስምና አድራሻ መያዝ አለበት፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ የአስማሚ ይሰየምልን ጥያቄን በተቀበለ በ፲ (በአስር) ቀናት ውስጥ መሰየም አለበት፡፡

### ፷፯. የአስማሚ መሰየምን ስለመቃወም

፩/ ማንኛውም ተከራካሪ ወገን በዚህ ደንብ አንቀጽ ፷፮ (፫) መሠረት በተሰጠ መሰየም ካልተስማማ አስማሚው በተሰየመ በ፭(በአምስት) ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ከነምክንያቱ በጽሁፍ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይችላል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ ስያሜውን በመቃወም የቀረበው ምክንያት አሳማኝ ሆኖ ካገኘው ተከራካሪ ወገኖች በስምምነት ሌላ ተተኪ ተሰያሚ ዕጩ እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

## CHAPTER TWO

## DISPUTE RESOULTION THROUGH MEDIATION

### 66. Appointment of Mediator

1/ When parties to a dispute fail to resolve their dispute amicably by themselves in acoordance with Article 64(1), one or both parties to the dispute may submit a request to the Authority for Appointment of Mediator.

2/ A request for Appointmént of Mediator submitted as per sub article (1) of this article shall contain:

a) the name, addresse of the parties to the dispute;

b) a brief explanation of the nature of the dispute and any specific relief sought; and

c) the name and address of the proposed mediator.

3/ The Authority shall appoint a mediator within 10 (ten) days after receipt of a request Appointment of Mediator.

### 67. Objection on the appointment of Mediator

1/ Any party to the dispute may who for good cause object the appointment of a mediator conducted pursuant to Article 66(3) this Regulation may submit is objection in written with its reason within 5 (five) days to the Authority.

2/ The Authority shall give instruction to the disputing parties to bring another proposed mediator when it finds the reason for objecting the appointment is reliable.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፪) መሠረት አስማሚ ምርጫ ሲያካሂዱ ተከራካሪ ወገኖች ሳይስማሙ ቀርተው ባለሥልጣኑ አስማሚ እንዲሰየምላቸው ከጠየቁ ባለሥልጣኑ ጥያቄው በቀረበ በ፭ (በአምስት) ቀናት ውስጥ ተተኪ አስማሚ በመመደብ ለተከራካሪ ወገኖች በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

## ፷፰. ማስማማትን ስለመጀመር

፩/ አስማሚው በተሾመ በ፲(በአስር) ቀናት ውስጥ ማስማማቱን መጀመር አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አስማሚው ሥራውን መጀመር እንዲችል ተከራካሪ ወገኖች ከአስማሚው ጋር የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## ፷፱. ከአስማሚነት ስለመልቀቅ ወይም ስለመነሳት

፩/ አስማሚው እንደተመደበ በሥራው ላይ አድልኦ ወይም ወገንተኛነት ሊፈጥሩ የሚችሉ ማናቸውም ምክንያቶች መኖራቸውን ከተረዳ ወዲያውኑ ሥራውን በመልቀቅ ለተከራካሪ ወገኖች እና ለባለሥልጣኑ ካሳወቀ በሌላ መተካት አለበት፡፡

፪/ አስማሚው በማናቸውም ጊዜ ነጻ ሆኖ ወይም ያለ ወገንተኛነት የመሥራት ችሎታውን ሊጎዱ የሚችሉ ወይም አግባብነት ባለው መንገድ ይጎዳሉ ተብለው የሚታሰቡ ማናቸውም ዓይነት ጥቅም ግጭት እንዳለው በተከራካሪ ወገኖች ተቃውሞ ሲቀርብና በባለሥልጣኑ ሲረጋገጥ ተነስቶ በሌላ መተካት አለበት፡፡

## ፸. ማስማማት ስለሚቋረጥበት ሁኔታ

፩/ የማስማማት ሂደት ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ ሊቋረጥ ይችላል:-

ሀ) ተከራካሪዎቹ አለመግባባታቸውን በስምምነት ከፈቱ ወይም ሊፈቱ ካልቻሉ፣

3/ If the parties fail to agree while conducting selection of mediator pursuant to sub article (2) of this Article and request the Authority to act on their behalf, the Authority shall replace a mediator and notify the parties in writing the replaced mediator within 5(five) days.

## 68. Commencing of Mediation

1/ The mediator shall commence mediation within 10(ten) days of appointment.

2/ The parties of such dispute shall be duty bound to cooperate with the mediator to commence the mediation before the lapse of time specified under sub-article (1) of this Article.

## 69. Resignation or Withdrawal of a Mediator

1/ The mediator shall replace by other if , after his appointment becomes aware of any circumstances that may create a bias, partiality or lack of neutrality he shall immediately resign and inform the parties to the dispute and the Authority.

2/ The Authority shall withdraw a mediator and replace by another mediator after being notified by one or both parties to the dispute, that the mediator shall be disqualified and when it is proved that he has any conflict of interest likely to affect or which might reasonably be perceived to affect the mediator's independence or ability to act impartially at all times.

## 70. Termination of Mediation

1/ The mediation shall terminate due to one of the following conditions:

a) when parties settle or fail to settle their disputes by agreement;

ለ) አስማሚው ከተከራካሪዎች ጋር ከተመካከረ በኋላ የማስማማት ሂደቱ ቢቀጥል ማስማማት የማይቻል መሆኑን ለተከራካሪዎች እና ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ ካሳወቀ፣ ወይም

ሐ) ከተከራካሪዎች አንዱ ወይም ሁሉም ምክንያት መግለጽ ሳያስፈልግ በራሳቸው ፍላጎት ማስማማቱ እንዲቋረጥ የወሰኑ መሆኑን ለአስማሚው እና ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ ካሳወቁ፡፡

፪/ አስማሚው በማስማማቱ የተደረሰበትን የመጨረሻ ውጤት ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## አለመግባባትን በግልግል ዳኝነት ስለመፍታት

### ፸፩. ስለግልግል ዳኝነት

በዚህ ደንብ መሠረት አለመግባባቱ በማስማማት ካልተፈታ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸው በባለስልጣኑ የግልግል ዳኝነት እንዲታይ ሊስማሙ ይችላሉ፡፡

### ፸፪. ስለግልግል ዳኝነት ፓናል መቋቋም

፩/ ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፸፩ መሠረት የሚቀርብ አለመግባባትን ለመፍታት የግልግል ዳኝነት ፓናል ያቋቁማል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቋቋመው የግልግል ዳኝነት ፓናል የዳኞች ብዛት ሰብሳቢውን ጨምሮ ከሦስት መብለጥ የለበትም፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም እንደ አለመግባባቱ የውስብስብነት ደረጃ ባለስልጣኑ በአንድ ዳኛ ብቻ እንዲዳኝ ሊወስን ይችላል፡፡

፬/ ባለሥልጣኑ ስለግልግል ዳኝነት ፓናል አባላት ብቃት፣ ሹመት፣ ሽረት እና መተካት በመመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

b) when the mediator, after consultation with the parties to the dispute, informs the authority and parties in writing that further attempts to secure outcome of agreement through mediation is no longer appropriate; or

c) if one or all parties to the dispute without a need to present reason, submit to the mediator and the Authority a written notice of their decision to the termination of the Mediation process .

2/ The mediator shall report the final result of the mediation in writing to the Authority.

## CHAPTER THREE

## DISPUTE RESOULTION THROUGH ARBITRATION

### 71. Arbitration

When the dispute is not settled through mediation pursuant to this Regulation the parties to the dispute may agree to submit their issue to the Authority for arbitration.

### 72. Establishment of Arbitration Panel

1/ The Authority shall establish an arbitration panel to resolve disputes submitted pursuant to Article 71 of this Regulation.

2/ The number of arbitrators of arbitration panel established pursuant to sub-article (1) of this Article, including the chairperson shall not exceed three.

3/ Notwithstanding the provision of sub-article (2) of this Article the Authority may, on the basis of the complexity of the issue, determine the issue to be arbitrated by one arbitrator.

4/ The Authority may issue a Directive to determine the qualification, appointment, cancellation and replacement of the members of the arbitration panel.

**፸፫. ስለግልግል ፓናል የዳኝነት ሥልጣን**

የግልግል ዳኝነት ፓናል በአዋጁ፣ በዚህ ደንብ እና ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ በሚሸፈኑ ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ሥልጣን አለው።

**፸፬. ስለግልግል ዳኝነት ፓናል ሥነ-ሥርዓት**

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፸፪ መሠረት በሚቋቋመው የግልግል ዳኝነት ፓናል በሚካሄድ ክርክር ላይ የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ተፈጻሚ ይሆናል።

**፸፭. ስለግልግል ዳኝነት የአገልግሎት ክፍያ**

ባለሥልጣኑ የግልግል ዳኞች አገልግሎት ክፍያን በተመለከተ በቀጥታ ጉዳዩ የሚመለከታቸውና ወጪውን በሚሸፍኑት አካላት ፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ በድርድር ይወስናል።

**ክፍል ሰባት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**፸፮. ስለ ጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እና የገንዘብ ቅጣት**

፩/ በኤሌክትሪክ አቅርቦት ላይ የተሰማራ የማመንጨት፣ የማስተላለፍ ወይም የማከፋፈልና እና የመሸጥ ባለፈቃድ አገልግሎት የሚሰጠው በተቀመጠለት ደረጃ መሠረት ያለመሆኑ ሲረጋገጥ ባለስልጣኑ ለባለፈቃዱ ከበቂ የማስተካከያ ጊዜ ጋር የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል።

፪/ በኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ አስገዳጅ አሠራሮች ላይ የአፈጻጸም ክፍተት ሲኖር፣ የብቃት ምስክር ወረቀት የተሰጣቸው ሙያተኞች፣ ፈቃድ ያላቸው የኢነርጂ ኦዲተሮች ወይም አማካሪዎች ወይም ኮንትራክተሮች አገልግሎት አሰጣጣቸው በተቀመጠለት ደረጃ ወይም ተቀባይነት ባለው አሠራር መሠረት ያለመሆኑ ሲረጋገጥ ባለሥልጣኑ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ከበቂ የማስተካከያ ጊዜ ጋር ይሰጣል።

**73. Jurisdiction of Arbitration Panel**

The arbitration panel shall have the jurisdiction on the matters covered by the Proclamation, this Regulation and directive to be issued .

**74. The Power Procedure of Arbitration Panel**

The Civil Procedure Code shall be applicable for the proceedings of the arbitration panel established in accordance of Article 72 of this Regulation.

**75. Arbitration Service Fee**

The Authority shall determine arbitration fee to be paid to arbitrators based on negotiation and consents of the parties directly involved in the case and who are paying for the service.

**PART SEVEN**

**MISCELLANEOUS PROVISIONS**

**76. Notice and Fine**

1/ Where it is ascertained that the generation, transmission, distribution and sales licensee is not providing service as per the determined service standard, the Authority shall issue written notice to the licensee and give sufficient time for corrective action.

2/ When gaps in the implementation of mandatory energy efficiency standards prevails; or services fall short of the standard issued or the generally accepted standard, by those professionals whose competency is certified or by licensed energy auditors, or licensed energy contractors, or licensed consultants, the Authority shall issue a written notice to those concerned, and give adequate time for corrective action.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በተሰጠ በቂ የማስተካከያ ጊዜ ውስጥ ባለፈቃዱ አገልግሎቱን በተፈለገው ደረጃ ባለማሻሻሉ በተገልጋዩ እና በኅብረተሰቡ ላይ ችግር ከተፈጠረ በአዋጁ አንቀጽ ፬ (፪) እና አንቀጽ ፰ (፪) መሠረት ባለስልጣኑ:-

ሀ) እንደጥፋቱ ክብደት እስከ ፲ ሚሊዮን (አስር ሚሊዮን) ብር የሚደርስ አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት ይወስናል፥

ለ) በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በአንድ ባለፈቃድ ላይ በዚህ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) መሠረት የሚጣለው ጠቅላላ የቅጣት መጠን ከብር ፳ ሚሊዮን (ሃያ ሚሊዮን) መብለጥ የለበትም፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በተሰጠ በቂ የማስተካከያ ጊዜ ውስጥ የሙያ ብቃት የተረጋገጠላቸው ፈቃድ ያላቸው የኢነርጂ ኦዲተሮች ወይም አማካሪዎች ወይም ኮንትራክተሮች የአገልግሎት ደረጃቸው በተቀመጠው ደረጃ ወይም በአዋጁ አንቀጽ ፬(፮) እንደተደነገገው በባለስልጣኑ በሚወጣ ኮድ መሠረት ያለመሆኑ ሲረጋገጥና ማስጠንቀቂያውን ተመስርቶ የማስተካከያ ወይም የእርምት እርምጃ ካልተወሰደ ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ ፬ (፪) መሠረት እስከ ብር ፪፻ሺ. (ሁለት መቶ ሺ.) የሚደርስ አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት ይወስናል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ባለሥልጣኑ የገንዘብ ቅጣት እርምጃ በሚወስድ ጊዜ በጥፋቱ ምክንያት የደረሰውን ጉዳት ከግምት ያስገባ መሆን አለበት፡፡

፮/ ባለስልጣኑ ቅጣቱን ከመወሰኑ በፊት ሊወሰን ያለውን ቅጣት አስመልክቶ ለባለጉዳዩ በመግለጽ መከላከያ ሀሳብ ካለው እንዲያቀርብ ወይም የማቅለያ ሀሳብ እንዲያቀርብ በቂ ጊዜ መስጠት አለበት፡፡

3/ if customers and community suffer due to failure to rectify or improve the service up to the level required within the rectification time limit provided under sub-article (1) of this Article,the Authority shall, in accordance with Article 4 (2) and Article 8 (2) of the Proclamation;

a) impose administrative penalty on the service provider based on the gravity of the fault up to Birr 10,000,000 (Ten Million);

b) provided, however, the total amount of the penalty to be imposed in one year on a licensee according to sub-article (3)(a) of this Article shall not exceed Birr 20,000,000 (Twenty Million);

4/ In accordance with sub-Article (2) of this Article, if no corrective action is taken following the notification and the services fall short of the standard issued or Code to be issued by the Authority in accordance with Article 4(6) of the Proclamation, by the holder of certificate of competence or by licensed energy auditors, or licensed energy contractors, or licensed consultants, the Authority shall impose administrative penalty on the service provider, in accordance with Article 4(2) of the Proclamation, up to Birr 200,000 (Two Hundred Thousand).

5/ The Authority when imposes penalty pursuant to this Article, it shall take in to account the damage materialized.

6/ The Authority shall, before deciding on the fine to be imposed, give an opportunity to the person subject to the fine with adequate time either to defend the proposed penalty or otherwise suggest reasons to mitigate the proposed penalty.

፯/ ዝርዝር የቅጣት እርከንና ዋስትና ሊሰጥባቸው የሚገቡ ዝቅተኛ የአገልግሎት ደረጃዎች ይህን ደንብ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፸፯. ስለጅምላ የኤሌክትሪክ ኃይል የግዥ ሥነ-ሥርዓት**

፩/ የጅምላ ኤሌክትሪክ ኃይል የሚገዛበት ሥነ-ሥርዓት አግባብ ባለው የሀገሪቱ ሕግ መሠረት በተቻለ መጠን ፍትሐዊ፣ ግልጽ እና ውድድርን የሚያበረታታ መሆን አለበት፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የጅምላ ኤሌክትሪክ ኃይል ግዥ አሠራር ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፫/ ለባለስልጣኑ ረቂቅ የጅምላ ኃይል ግዥ እና ረቂቅ የኔትወርክ አጠቃቀም ስምምነት በአዋጁ አንቀጽ ፬ (፯) መሠረት ሲቀርብለት መርምሮ ያፀድቃል፡፡

**፸፰. ስለ ደህንነት፣ ቴክኒክ እና የአገልግሎት ጥራት ደረጃዎች**

ባለሥልጣኑ ስለ ደህንነት፣ ቴክኒክና የአገልግሎት ጥራት ደረጃዎች መመሪያ ያወጣል፡፡

**፸፱. አደጋን ስለማሳወቅ**

፩/ የኤሌክትሪክ ኃይል ከማመንጨት፣ ከማስተላለፍ፣ ከማከፋፈል ወይም ከመጠቀም ጋር በተገናኘ ለሰው ሕይወት ማለፍ ምክንያት የሆነ ወይም ከባድ የአካል ጉዳት ያደረሰ ወይም በንብረት ላይ ከባድ ውድመት ያደረሰን ማናቸውንም አደጋ ባለፈቃዱ ባወቀ በ፳፬ ሰዓት ውስጥ ለባለሥልጣኑ እና አግባብ ላለው የመንግሥት አካል ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡



7/ The detail level of penalty and minimum service levels to be guaranteed for the implementation of this Article shall be determined by a directive to be issued to implement this Regulation.

**77. Procedure for Bulk Electric Power Procurement**

1/ The procedure for bulk electric power procurement shall, as far as practicable, be in accordance with the relevant law of the country, equitable, transparent, and competitive.

2/ The Authority may issue directive on the procedure of bulk power procurement process pursuant to sub-article (1) of this Article.

3/ The Authority shall examine and approve draft power purchase agreement and draft network use agreement when presented to it pursuant to Article 4(7) of the Proclamation.

**78. Standards of Safety, Technical and Quality of Service**

The Authority shall issue a directive on standards of safety, technical and quality of service.

**79. Accident Reporting**

1/ If any accident occurs in connection generation, transmission, distribution or use of electrical energy resulting in serious injury to or loss of life of a human being or serious physical damage to a property, the licensee shall send to the appropriate government organ and the Authority, a report of the accident within 24 hours when he has knowledge of its occurrence.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከባድ የአካል ጉዳት ማለት ተጎጂው በሆስፒታል ተኝቶ የሚታከም ሲሆን እንዲሁም ከባድ የንብረት ጉዳት ማለት አብዛኛው የንብረቱ ክፍል የተበላሸ ወይም የወደመ እንደሆነ ነው፡፡

2/ Pursuant to sub-article (1) of this Article, serious injury means injury that requires the victim to become an in-patient at a hospital, and serious physical damage to a property means that a significant part of the property has been damaged or destroyed.

## ፹. በባለሥልጣኑ ስለሚደረግ ምርመራ

፩/ ማንኛውም በባለሥልጣኑ የተወከለ ተቆጣጣሪ በባለፈቃዱ ይዞታ በሆነ በማንኛውም ቦታ ውስጥ የመግባት እና በማናቸውም ጊዜ የመቆጣጠር፣ የመመርመር እንዲሁም መረጃ የመውሰድ መብት አለው፡፡

፪/ ባለፈቃዱ በቁጥጥር እና በምርመራ ወቅት በባለሥልጣኑ ከተወከለው ተቆጣጣሪ ጋር መተባበር እና ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡

፫/ በባለሥልጣኑ የተወከለ ተቆጣጣሪ የቁጥጥር ተግባሩን ከመጀመሩ በፊት ከባለሥልጣኑ የተሰጠውን የተቆጣጣሪነት መታወቂያ ካርድ ወይንም አግባብነት ያለውን ፈቃድ ማሳየት አለበት፡፡

## 80. Inspections by the Authority

1/ Any duly authorized officer by the Authority shall have the right of access to the premises and operational areas of the licensee and be entitled at all times to inspect and to make examinations and tests of a licensee's works.

2/ In the course of such inspection the licensee shall cooperate with and render assistance to such duly authorized officer by the Authority.

3/ The duly authorized officer shall show his identity card or appropriate license issued by the Authority for such purpose before commencing inspection activities.

## ፹፩. ከግሪድ ውጭ የማከፋፈል፣ የመሸጥ እና የማመንጨት ባለፈቃድ ስለሚደረግ ጥበቃ

፩/ ብሔራዊ ግሪዱ ከግሪድ ውጭ ከሚሰራ የማመንጨት፣ የማስተላለፍ ወይም የማከፋፈል እና የመሸጥ የብቻ የሆነ ባለፈቃድ ኔትወርክ ዘንድ በሚደርስበት ወቅት የብሔራዊ ግሪዱ ባለፈቃድ በስምምነት አግባብነት ያለው ካሳ ለባለፈቃዱ በመክፈል የማከፋፈል እና የመሸጥ የብቻ ፈቃድ ኔትወርኩንና እና ተያይዞ ያለውን የማመንጫ ፋሲሊቲ ከብሔራዊ ግሪዱ ጋር እንዲጠቃለል ሊያደርግ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተጠቀሰው መሠረት የአቅርቦት ፋሲሊቲው ወደ ብሔራዊ ግሪዱ የሚካተተው ደረጃውን ጠብቆ የተሰራ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

## 81. Protection of Off-Grid Distribution Sale, and Generation Licensee

1/ In the event that the national grid reaches to the off-grid exclusive generation, transmission or distribution and sale licensee's network, the national grid licensee, operating under exclusive license may, by agreement, integrate such distribution and sale network and related generation facilities upon payment of reasonable compensation to the respective licensee and integrate it to the national grid.

2/ The supply facility to be integrate to the national grid pursuant to sub-article (1) of this article shall technically be qualified to integrate it to the national grid.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከፈለውን የካሳ መጠን አስመልክቶ ስምምነት ላይ ካልተደረሰ ባለሥልጣኑ በግልግል ዳኝነት አይቶ ይወስናል፡፡

፬/ ከግሪድ ውጭ ያለ የማከፋፈል እና የመሸጥ ባለፈቃድ በመፍረሱ ወይም በመክሰሩ ምክንያት የኤሌክትሪክ አገልግሎት መስጠት ያልቻለ እንደሆነ የነባር ደንበኞች አገልግሎት እንዳይቋረጥ ለማድረግ የብሔራዊ ግሪዱ እንዳስፈላጊነቱ የማስተላለፍ ወይም የማከፋፈልና የመሸጥ ባለፈቃድ ከግሪድ ውጭ ያለውን የማመንጫና የማከፋፈያ ፋሲሊቲ እንዲያገናኝ ባለሥልጣኑ ውሣኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**፹፪. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ባለሥልጣኑ ይህን ደንብ በአግባቡ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፹፫. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

፩/ ይህ ደንብ ከመጽናቱ በፊት ለንግድ ዓላማ የተሰጠ ኤሌክትሪክ የማመንጨት፣ የማስተላለፍ ወይም የማከፋፈልና የመሸጥ ወይም የአስመጪነት እና የላኪነት ፈቃድ በባለሥልጣኑ በማስታወቂያ በሚገለጸው የጊዜ ገደብ ውስጥ በዚህ ደንብ መሠረት በሚሰጥ አዲስ ፈቃድ መተካት አለበት፡፡

፪/ ይህ ደንብ ከመጽናቱ በፊት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በዚህ ደንብ መሠረት በባለሥልጣኑ ማስታወቂያ በሚገለጽ የጊዜ ገደብ ውስጥ በአዲስ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እስኪተካ ድረስ ጸንቶ ይቆያል፡፡

3/ In the event of disagreement over the amount of compensation to be paid for integration pursuant to sub-article (1) of this Article, the Authority shall settle the issue through arbitration.

4/ The Authority may give a decision that the national grid to connect the off-grid generation and transmission facility from the transmission or distribution and sale licensee to supply electricity to those customers who are without a regular supply of electricity because of the liquidation or bankruptcy of the existing off-grid distribution and sale licensee.

**82. Power to Issue Directive**

The Authority may issue directives for the proper implementation of this Regulation.

**83. Transitional Provisions**

1/ Any person engaged in the operations of generation, transmission or distribution and sale, import or export of electricity for commercial purpose prior to the coming into force of this Regulation shall, within the period to be specified by the notice of the Authority, replace his license with new license to be issued in accordance with this Regulation.

2/ Any certificate of competency of electrical contractors issued by the Authority prior to the coming into force of this Regulation shall remain valid until replaced by a new certificate of competency issued pursuant to this Regulation within the period to be specified by the notice of the Authority.

**፹፬. <u>የተሻሩ እና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>**

፩/ የኤሌክትሪክ ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵፱/፲፱፻፺፩ ተሽሯል፡፡

፪/ ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፹፭. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር ፳ ቀን ፪ሺ፲፩ዓ.ም**

**ዶ/ር አብይ አህመድ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**84. <u>Repealed and Inapplicable Laws</u>**

1/ The Electricity Operations Council of Ministers Regulation No. 49/1999 is hereby repealed.

2/ No Regulation, directive or practice which is inconsistent with this Regulation shall have effect with respect to matters covered in this Regulation.

**85. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa this 28th Day of January,2019**

**ABIY AHMED (DR.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

## ሠንጠረዥ ፩

ለፈቃድ እና ለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ የክፍያ ዝርዝር

| ፩. ለቁጥጥር/ ለሬጉሌሽን የአገልግሎት ክፍያ | | |
|---|---|---|
| ተ.ቁ | የአገልግሎት ዓይነት | ለአገልግሎቱ የሚከፍለው ክፍያ መጠን በብር |
| ፩ | የኤሌክትሪክ ዘርፍ ቁጥጥር አገልግሎት | 0.117 ብር/ በተሸጠ ሜጋ ዋት ሰዓት በዓመት |
| **፪ የኤሌክትሪክ ሥራ ፍቃድ ክፍያ** | | |
| ተ.ቁ | የአገልግሎት ዓይነት | ለአገልግሎቱ የሚከፍለው ክፍያ መጠን በብር |
| ፩ | የኤሌክትሪክ ማመንጨት/ማስተላለፍ/ ማከፋፈልና መሸጥ ፈቃድ ማመልከቻ | 496 |
| ፪ | የኤሌክትሪክ ማመንጨት/ማስተላለፍ/ ማከፋፈልና መሸጥ ፈቃድ መስጠት | |
| | እስከ 10 ሜጋዋት | 2500 |
| | ከ10 ሜጋዋት በላይ | 6883 |
| ፫ | የማመንጫ/ማስተላለፊያ /ማከፋፈያና መሸጥ ፈቃድ ዕድሳት /ማሻሻል/ማስተላለፍ | |
| | እስከ 10 ሜጋዋት | 1668 |
| | ከ10 ሜጋዋት በላይ | 4595 |

| ፫. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የአገልግሎት ክፍያ | | |
|---|---|---|
| ፫.፩ በባለሙያ የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ | | |
| የሙያ ደረጃ | የአገልግሎት ዓይነት | ለአገልግሎቱ የሚከፍለው ክፍያ መጠን በብር |
| ደረጃ ፩ | ምዝገባ | 51.56 |
| | የጽሁፍ ፈተና | 212.32 |
| | የተግባር ፈተና | 272.98 |
| | ሰርተፍኬት | 69.76 |
| | እድሳት | 121.33 |
| ደረጃ ፪ | ምዝገባ | 41.25 |
| | የጽሁፍ ፈተና | 169.85 |
| | የተግባር ፈተና | 218.39 |
| | ሰርተፍኬት | 55.81 |
| | እድሳት | 97.06 |
| ደረጃ ፫ | ምዝገባ | 30.95 |
| | የጽሁፍ ፈተና | 127.39 |
| | የተግባር ፈተና | 163.79 |
| | ሰርተፍኬት | 41.85 |
| | እድሳት | 72.80 |
| ደረጃ ፬ | ምዝገባ | 20.63 |
| | የጽሁፍ ፈተና | 84.93 |
| | የተግባር ፈተና | 109.20 |
| | ሰርተፍኬት | 27.90 |
| | እድሳት | 48.53 |
| ደረጃ ፭ | ምዝገባ | 10.30 |
| | የጽሁፍ ፈተና | 42.46 |
| | የተግባር ፈተና | 54.60 |
| | ሰርተፍኬት | 13.95 |
| | እድሳት | 24.27 |

## Table 1

Fee for issuance of license and competency certification

| 1.Regulation service fee | | |
|---|---|---|
| No. | Service type | Service fee amount in birr |
| 1 | Electricity sector regulatory service | 0.117 per MWH sold energy per year |
| **2.Electricity operation license fee** | | |
| No. | Service type | Service fee amount in birr |
| 1 | Generation/transmission/distribution and sales license application | 496 |
| 2 | Generation/transmission/distribution and sales license issuance | |
| | Upto 10 MW | 2500 |
| | Above 10 MW | 6883 |
| 3 | Generation/transmission/distribution and sales license renewal, upgrade and transfer | |
| | Up to 10 MW | 1668 |
| | Above 10 MW | 4595 |

| 3. Competency certification service fee | | |
|---|---|---|
| 3.1. Competency certificate for individuals | | |
| Grade of competency | Service type | Service fee amount in birr |
| Grade 1 | Registration | 51.56 |
| | Theory exam | 212.32 |
| | Practical exam | 272.98 |
| | Certificate | 69.76 |
| | Certificate renewal | 121.33 |
| Grade 2 | Registration | 41.25 |
| | Theory exam | 169.85 |
| | Practical exam | 218.39 |
| | Certificate | 55.81 |
| | Certificate renewal | 97.06 |
| Grade 3 | Registration | 30.95 |
| | Theory exam | 127.39 |
| | Practical exam | 163.79 |
| | Certificate | 41.85 |
| | Certificate renewal | 72.80 |
| Grade 4 | Registration | 20.63 |
| | Theory exam | 84.93 |
| | Practical exam | 109.20 |
| | Certificate | 27.90 |
| | Certificate renewal | 48.53 |
| Grade 5 | Registration | 10.30 |
| | Theory exam | 42.46 |
| | Practical exam | 54.60 |
| | Certificate | 13.95 |
| | Certificate renewal | 24.27 |

፫.፪ በድርጅቶች ለብቃት ማረጋገጫ የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ

| ደረጃ | የአገልግሎት ዓይነት | ለአገልግሎቱ የሚከፍለው ክፍያ መጠን በብር |
|---|---|---|
| ደረጃ ፩ | የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት | 606.64 |
| | የብቃት ማረጋገጫ ለማደስ | 121.33 |
| ደረጃ ፪ | የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት | 400.38 |
| | የብቃት ማረጋገጫ ለማደስ | 80.08 |
| ደረጃ ፫ | የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት | 200.19 |
| | የብቃት ማረጋገጫ ለማደስ | 40.04 |

፬. የኢነርጂ ኦዲተሮችና ለኢነርጂ አገልግሎት ሰጪ ኩባንያዎች ፈቃድ የአገልግሎት ክፍያ

| | የአገልግሎት ዓይነት | ለአገልግሎቱ የሚከፍለው ክፍያ መጠን በብር |
|---|---|---|
| ለኢነርጂ ኦዲተሮች | ለፍቃድ ማመልከቻ | 321.5 |
| | ፍቃድ ለመስጠት | 402 |
| | ፍቃድ ለማደስ | 143 |
| ለኢነርጂ አገልግሎት ሰጪ ኩባንያዎች (ESCOs) ፈቃድ | ለፍቃድ ማመልከቻ | 68 |
| | ፍቃድ ለመስጠት | 163 |
| | ፍቃድ ለማደስ | 40.75 |

3.2 Cervise fee for Competency certificate for companies

| Grade of competency | Service type | Service fee amount in birr |
|---|---|---|
| Grade 1 | Certificate | 606.64 |
| | Certificate renewal | 121.33 |
| Grade 2 | Certificate | 400.38 |
| | Certificate renewal | 80.08 |
| Grade 3 | Certificate | 200.19 |
| | Certificate renewal | 40.04 |

4. Energy Auditors and energy service company license

| | Service type | Service fee amount in birr |
|---|---|---|
| Energy Auditors | Application | 321.5 |
| | License | 402 |
| | License renewal | 143 |
| Energy Service providing Companies (ESCOs) | Application | 68 |
| | License | 163 |
| | License renewal | 40.75 |

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት